# በላንድስኬፕ አርኪቴክት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ



ኢንጂነር ጌታቸው ማህተመሥላሴ

2004 ዓ.ም.


<u>አዘጋጅ</u>
እመቤት ዘውዴ

# *Landscape Architecture*

***The Arrangement of Earth and the Objects on it for Man's use and its Beauty!!***

# ላንድስኬፕ አርክቴክቸር

**መልክአ ምድርንና በላዩ ላይ ያሉ ነገሮችን አዋህዶ ለሰው ልጅ አገልግሎት ከውበት ጋር የሚያመቻች**

አንደኛ እትም

አሳታሚ፡- ኤሚ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ፕሮሞሽን ሰርቪስ ኃ.የተ.የግል ማህበር

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::
2004 ዓ.ም.

__አዘጋጅ__
እመቤት ዘውዴ

__የውስጥ ዲዛይን፣ የገፅ ቅንብርና ትየባ__
__ሰውነት ኃይለማርያም__

# ምስጋና

ይህንን መጽሐፍ በምናሳትምበት ወቅት የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ (ዶ/ር) እና አስተዳደሩ ለኢንጂነር ጌታቸው ማህተመ ሥላሴ ያላቸውን ክብር የገለፁበት ድጋፍ ስላደረጉ በባለታሪኩና በኤሚ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ፕሮሞሽን ሰርቪስ ስም ላቅ ያለ ምስጋና ይድረሳቸው።

# መግቢያ

ጥቂት የማይባሉ ባለሙያዎች ለኢትዮጵያ ሃገራቸው ድንቃ ድንቅ የሆኑ ሥራዎችን ሠርተው ማለፋቸው ቢታወቅም፣ የብዙዎቹ ኢትዮጵያውያኖች ሥራዎችና ማንነት በጽሁፍ ተመዝግቦ ለተከታዩ ትውልድ አልተላለፉም።

ኢትዮጵያ አሁን ያላትን የሥልጣኔ ገጽታ እንዲኖራት ያደረጉ ታላላቅ ኢትዮጵያውያን እንደ ሌላው የዓለም ታዋቂ ሰዎች ሥማቸውና ሥራዎቻቸው በተከታዩ ትውልድ ተገቢ ቦታቸውን አላገኙም። ይህም ሊሆን ከቻለበት ምክንያት አንዱ ሥራዎቻቸውና ማንነታቸው በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ባለመቆየቱ ነው።

በተመሳሳይ አዲስ አበባ አሁን ያላትን የከተማነት ገጽታ እንድታገኝ ያደረጉ ባለሙያዎች ነበርዋት አሏትም። ሥማቸውና ሥራ ዎቻቸው በታሪክ ተመዝግቦ የሚገኙት ግን ጥቂቶች ናቸው።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ከላይ የተገለፀውን ሃሳብ መሠረት በማድረግ አዲስ አበባ አሁን እደረሰችበት ደረጃ ካደረሷት ባለሙያዎች አንዱ የሆኑትን የኢንጂነር ጌታቸው ማህተመ ሥላሴን ታሪክ ማሳወቅና ማስተላለፍ ነው።

የእርሻ ባለሙያ እንዲሁም በላንድስኬፕ አርክቴክት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ባለሙያ የሆኑና በታውን ፕላኒንግ ሙያ በ6ኛ ደረጃ ላይ የተቀመጡት ኢንጂነር ጌታቸው ለአዲስ አበባ የከተማነት መልክ መያዝ ያደረጉት አንኳር አስተዋጽኦ በዚህ የግል ህይወታቸውን በሚተርከው መጽሐፍ ውስጥ ቀርቧል።

ኢንጂነር ጌታቸው በግብርናና በምህንድስና ሙያቸው በተለያዩ ጊዜአቶች ለሃገራቸው ለኢትዮጵያ ያደረጉትን አስተዋጽኦ በመመልከት፣ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥም የሰጡዋቸውን አገልግሎቶች በማጤን፣ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እየሰጡ ያሉትን ነፃ አገልግሎት በማስተዋል ትውልድ ብዙ ይማራል ብለን እንገምታለን።

መልካም ንባብ

# የባለታሪኩ ልዩ ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ መሰረት ያደረገው በግለሰብ ታሪክ ላይ በመሆኑ እውነታዎች ተጓድለው ቢገኙ በአንባቢዎች ዘንድ ታሪኩ ታማኝነትን ሊያጣ ስለሚችል ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግን ይጠይቃል።

ይህንንም ጨዋነት ልማር የቻልኩት ከአባቴ ከክቡር ብላቴን ጌታ ማሕተመ ሥላሴ ወ/መስቀል ከራሳቸውና ከጻፏቸው በርካታ መጽሐፎች ነው።

አባቴ ክቡር ብላቴን ጌታ ማህተመ ሥላሴ እኔን ተንከባክበው አሳድገው፣ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ አስተምረው፣ ለከፍተኛ የሥራ ደረጃ አብቅተው፣ ድረው፣ የጎጆ መውጫዬን አመቻችተው፣ በሕይወት እያሉ ባደረጉት ኑዛዜአቸው ሳይቀር እገሌ ተገሌ ሳይሉ ሳያበላልጡ ያለ ንብረታቸውን ለሁላችንም እኩል እንድንወርስ ያደረጉ አርቆ አስተዋይ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው የሁላችንም አባት ስለሆኑ ባባትነታቸው አሁንም አመልክባቸዋለሁ።

ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት ታሪክን ላለማዛባትና ልጆቼም ሊያውቁት የሚገባውን ለማሳወቅ ስል ብቻ ከዚህ ቀጥሎ ያለው በሕይወት ታሪኬ ውስጥ እንዲጠቀስ አድርጌአለሁ።

የኔ የጌታቸው ወላጅ አባት አቶ ተክለማሪያም ኃይለሥላሴ ይባላሉ የእናቴ የወይዘሮ አምሳለወርቅ ክፈተው ሁለተኛ ሕጋዊ ባል ነበሩ።

አቶ ተክለማሪያም ኃይለሥላሴ የሐረር ተወላጅ ሲሆኑ የቀድሞ የሐረርጌ ንጉስ የነበሩት የአሚር አብዱላሂ የልጅ ልጅ ነበሩ።

እናታቸውም ወ/ሮ ደስታ ሲሆኑ የክርስትና ኃይማኖት ተከታይ የሆኑት ከጨለንቆ ጦርነት በኂላ ሲሆን የአቶ ኃይለሥላሴ የክርስትና አባት ልዑል ራስ መኮንን ሲሆኑ የወ/ሮ ደስታ ክርስትና እናት ደግሞ ክብርት ወ/ሮ የሺእመቤት ናቸው፡፡ የልጃቸው የአቶ ተክለማርያም ኃይለሥላሴ የክርስትና አባት ደግሞ ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ሲሆኑ ከጨለንቆ ጦርነት በኂላ ፍቅርንና ሰላምን ለመፍጠር ሲሉ የነበረውን የሃገር ባህል በመጠቀም በኃይማኖት ተሳሰሩ፡፡ እኔም ጌታቸው በደም የተጋራኂቸው አባቴና የወላጅ እናቴን የወ/ሮ አምሳለወርቅን የክርስትና ኃይማኖት ከሕፃንነቴ ጀምሮ በመከተል ከአባቴ ከክቡር ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ፤ ከእናቴ ከወ/ሮ አምሳለወርቅ ክፈተው ከእህቶቼና ከወንድሞቼ ጋር በፍቅር አብሬ ስለምኖር ፈጣሪዬ የሞቱትን ነፍሳቸውን እንዲምርልኝ በሕይወት ያለነውንም እንደቸርነቱ በደህና እንዲጠብቀን የየቀኑ ጸሎቴ ነው፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው ማህተመሥላሴ

መስከረም 30 ቀን 2004 ዓ.ም.



# ምዕራፍ አንድ
# የልጅነት ግዜ

በ1921 የተወለዱት ኢንጂነር ጌታቸው ለወ/ሮ አምሳለወርቅ ክፈተው ሁለተኛ ልጅ ናቸው፡፡ የእርሳቸው ታላቅ ወንድም ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ ሲሆኑ ቀሪዎቹ የእሳቸው ተከታይ ወንድሞቻቸው ደግሞ አቶ ሰለሞን ማህተመሥላሴ፣ አቶ ታሪኩ ማህተመሥላሴ፣ አቶ በለጠ ማህተመሥላሴና አቶ ግርማ ማህተመሥላሴ ናቸው፡፡ ሴት እህቶቻቸው ናርዶስ ማህተመሥላሴ፣ ሃረገወይን ማህተመሥላሴ፣ ጌጤነሽ ማህተመሥላሴና ወ/ሮ ወላንሳ ማህተመሥላሴ ናቸው፡፡

ታላቅ ወንድማቸው ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ የአፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት ከሥልጣን ያወረደው ወታደራዊው የደርግ መንግሥት ሥልጣን እንደያዘ ለአምስት ዓመት ያህል በእሥር ካቆያቸው በኂላ ከሌሎች ከእሳቸው ጋር አብሮ ካሠራቸው ሚኒስትሮችና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች እንዲሁም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዮፍሎስ፣ ፓትሪያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያን፣ አቶ አበበ ከበደ፣ አቶ አሰፋ ድፋዬ፣ ክቡር ደጃዝማች ሐረጎትንና ደጃዝማች ካሣ ወልደማርያም ጋር በገመድ እየታነቁ እንዲገደሉ አድርጓል፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው በ1966 ዓ.ም ከወንድማቸው ከክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴና ከአባታቸው ከክቡር ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ ወ/መስቀል ጋር በደርግ ታሥረዋል፡፡ ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ በዛው በእሥር ቤት እንዳሉ ነው ህይወታቸው ያለፈው፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ ለታላቅ ወንድማቸው ለክቡር

አቶ ሰይፉ ማህተመስላሴ ከፍተኛ ፍቅር፣ አክብሮትና አድናቆት ነበራቸው። በመሠረቱ ክቡር አቶ ሰይፉ በኢትዮጵያ አብይ ከሆኑ የሥልጣኔ አራማጆች ውስጥ ዋነኛ ተሳታፊ ብቻ በመሆን ሳይወሰኑ፣ ሌሎች እንዲሳተፉና ለሃገራቸው የሚጠበቅባቸውን የሃላፊነት ሚና እንዲጫወቱ ሁኔታዎችን ያመቻቹ ታላቅ ሰው ነበሩ።

ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ ከአሜሪካን ሃገር ከጉስታቮስ አድ ልፋስ ኮሌጅ በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ በዲግሪ ተመርቀዋል። ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ብርሃን ተቋዳሽ እንድትሆን ካስቻልዋት ጠንካራ የሥራ ሰዎች ውስጥ አንዱ ናቸው። በሥራቸውም ጠንካራ የሙያ ሰዎችም ነበርዋቸው፣ እንደ ወንድምም እንደ ጓደኛም የሚያሠሩዋቸው።

ብዙዎቹ የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቦች ጥናት የተሠሩት በእሳቸውና በባልደረቦቻቸው በተለይም እንደ እነ አቶ አሰፋ ጥላሁን በመሰሉ ባለሙያዎች ነው። ከጥናቶቹ መካከል በዋናነት የአዋሽ፣ የቆቃና የባህር ዳር እንዲሁም የፊንጫ ግድቦች ተጠቃሾች ናቸው።

ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ በዋናነት በመብራት ሃይል፣ በሚኒስትር ማዕረግ በሥራና መገናኛ እንዲሁም በደርግ መንግሥት ከመታሠራቸው በፊት የትምህርት ሚንስቴር ሚንስትር ሆነው ሰርተዋል። የሚያስገርመው ነገር ለአገር መታወክና ለእሳቸውም ለእሥር መዳረግ ምክንያት የነበረው ሴክተር ሪቪዩ በአሁኑ ጊዜ እየተሸራረፈም ቢሆን በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፣ ለእሳቸው ግን የሞታቸው ጦስ እስከመሆን ደርሷል።

ኢንጂነር ጌታቸው እራሳቸው እንደሚናገሩት፣ አባታቸው ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ መላ ጊዜያቸውን ከሥራና ጥናት ነክ ከሆኑ





ሙያዎች ጋር የተጣመረ በመሆኑ ቀረቤታቸው ሲበዛ እሳቸው ከአባታቸው ጋር ሳይሆን ከክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ ጋር ነበር ማለት ይቻላል።

የኢንጂነር ጌታቸው አባት ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ በፈረንሳይ ሃገር በሶባርን ዩኒቨርሲቲ የአፈርና የእርሻ ምርምር ሙያ በመከታተል በአግሮ ኢኮኖሚ የተመረቁ ሊቅ ናቸው። ለአገርና ለትውልድ ጠቃሚ የሆኑ ከ18 በላይ መጽሐፍትን ደርሰው ለንባብ አብቅተዋል።

ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ በሙያቸው ካበረከቱዋቸው አስተዋ ፅኦዎች በተጨማሪ በርካታ ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ሥራዎች ሰርተዋል። ገና ከውጭ ሃገር ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ቀጥታ ወደ ሥራ ነበር የገቡት።

በርበሬ በስፋትና በብዛት የሚመረትበትን ዘዴ በመጀመሪያ የቀየሱት ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ መሆናቸው ይነገራል። ትልቅና ሰፊ የበርበሬ እርሻን እንደተአምር በመፍጠር ቀደም ብሎ በውስን ደረጃ ይመረት የነበረውን በርበሬ በስፋት እንዲመረት ለማድረግ ተችሎ ነበር። በስፋት እንዲመረት የተደረገው በርበሬ ለቤተ መንግሥትም ይቀርብ ነበር።

ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ ከእርሻው ባሻገርም ወደ መንገድ ሥራም ገብተዋል። በእሳቸው እገዛም ነበር ከአዲስ ዓለም እስከ ጌዶ ያለው መንገድ የተቀየሰው። እንዲሁም የሠንቀሌን ድንጋይ ለዘመናዊ ሥራ ያበቁት እሳቸው ነበሩ።

ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ ወ/መስቀል መላ ግዜያቸውን በሥራ ስለጠመዱት የቤተሰቡና፣ የማህበራዊ ህይወቱ ሃላፊነት የወደቀው በወ/ሮ አምሳለ ወርቅ ክፈተው ሙያና ሁለገብነት ነበር ማለት

ይቻላል፡፡ ወይዘሮ አምሳለ ወርቅ ከንጉሥ ሳህለ ሥላሴ የዘር ሃረግ ከሚወለዱት የክቡር ደጃዝማች ክፈተው ደባልቄ ልጅ ናቸው፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው እናታቸው ጥሩና ባለሙያ ስለመሆናቸው በስሜትና በፍቅር ነው የሚናገሩት፡፡ ወ/ሮ አምሳለወርቅ እናትነታቸው ከማህጸናቸው ለወጡት ለልጆቻቸው ብቻ አልነ በረም፡፡ በዝምድናና በመተዋወቅ ወደ ቤታቸው አምጥተው ላሳደጓቸውና ለቁም ነገር ላበቋቸው ልጆችም ጥሩ እናትነታቸውን አስመስክረዋል፡፡ ያሳደጓቸው ልጆችም እከሌ ማህተመሥላሴ፣ እከሊት ማህተመሥላሴ ይባላሉ እንጂ በሌላ የአባት ሥም አይጠሩም፡፡

የኢንጂነር ጌታቸው የልጅነት ቤታቸው በእናታቸው ቸርነትና ደግነት የተነሳ ቀኑን ሙሉ ገበታ ሆኖ ነበር የሚውለው፡፡ እናትየው የጣዱት ወጥ ከምድጃው ላይ ሳይወርድ እዛው እንደተጣደ በጉርሻና በጭልፋ ተሟጦ ያልቃል፡፡ እናት የቤቱን ልጆች ሥም ተራ በተራ በመጥራት “እከልዬ ና እስቲ ቀረብ በል….እከሌ ዛሬ የት ጠፋ አላየሁትምሳ…. እስቲ እባካችሁ ፈልጉት” እየተባለ የእናትን ጉርሻ መጉረስ ነበር፡፡

የኢንጂነር ጌታቸው ቤት ሥርዓት የሌለውና የተዝረከረከ አልነበረም፡፡ የሃገር ልማድና ወግ የሚጠይቀውን የሥነ-ምግባር ግዴታ ልቅም ተደርጎ የሚተገበርበት ነበር ቤቱ፡፡ ታላቅን የማክበር፣ትህትናን የማስቀደምና የዛ የቤተሰብ አባል የሆነ ልጅ ነገ መልካም ሰው ሆኖ “ለክብርና ለማዕረግ ያብቃህ!” የሚለውን ምርቃት የሚጎናፀፍበት ቤት ነበር፡፡

በግዜው የልጆች ሥነ-ምግባር መልካም ገጽታ እንዲኖረው አድርጎ ለመቅረጽ የሚሳተፈው ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ነበር ማለት





ይቻላል፡፡ አባት፣ እናት፣ ዘመድ አዝማድ፣ ጎረቤትና በመንገድ የሚጓዘው ትላልቁ ሰው ልጁን አወቀው አላወቀው ይሳተፋል፤ እያመሰገነም፣ እየተቆጣም፣ እየቆነጠጠም፣ እየኮረኮመም፡፡ “በዚህ ሂደት ውስጥ በማደጌ ነው ለዚህ ደረጃ የበቃሁት” ይላሉ ኢንጂነር ጌታቸው፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው የሥነ-ሥርዓቱን ጠቀሜታና ምንጩን ሰፋ አድርገው ገልፀውታል፡፡ “አያታችን ክቡር ፀሃፊ ትዕዛዝ ወ/መስቀል በቤተ መንግሥት ሥርዓት አከባበር ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ያንንም ሥርዓት ነበር በቤታችን ውስጥ እንዲተገበር ያደረጉት፡፡ ያም ሥነ-ሥርዓትና ሥነ-ምግባር ከልጅ ልጅ እንዲተ ላለፍም ጥረዋል፡፡ አዋቂ ሰዎች በሚናገሩበት ጊዜ ጣልቃ ገብቶ መናገር ጨርሶ አይታሰብም ነበር፡፡ በቤታችን የቀሰምነው ሥነ-ምግባር ለኑሯችንና ለአስተሳሰባችን ጠቅሞናል፡፡ በዛን ጊዜ ለእነሱ ያሳየነው ሥነ-ሥርዓት፣ ለእኛ ተላልፏል፡፡ አሁን ግን ተቀባይ ያገኘ አይመስለኝም፡፡ የሚያሳዝነውም ይሄ ነው፡፡ ዛሬ ዛሬ ሰዎች ሌላውን ቢያከብሩ ነገ እነሱ እንደሚከበሩ የተገነዘቡት አይመስለኝም፡፡ ለእነሱ ለእራሳቸው መንገድ ማበጀታቸው መሆኑን አልተረዱትም፡፡ እንዲህ ዓይነት ጥብቅ ሥነ-ሥርዓት ያለበት ቤት ነበር ቤታችን፡፡”

ኢንጂነር ጌታቸው በልጅነታቸው ያደጉት የእናታቸው ታላቅ እህት ከሆኑት ከአክስታቸው ከወ/ሮ ሮማን ወርቅ ጋር ነበር፡፡ ወ/ሮ ሮማን ወርቅ የደጃች አባሻውል ባለቤት ነበሩ፡፡ የቄስ ትምህርትም የጀመሩት እዚሁ አክስታቸው ቤት ሳሉ ነበር፡፡

ደጃች አባሻውል ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ ሲሞቱ፣ ኢንጂነር ጌታቸው ትምህርታቸውን ለመቀጠል እንዲያመቻቸው

በማለት ወደ ወላጆቻቸው ቤት ተመለሱ።

በዛን ጊዜ ክቡር ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ የልዑል አልጋወራሽ እንደራሴ ሆነው ይሰሩ ነበር። ኢንጂነር ጌታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት ደሴ በሚገኘው በወ/ሮ ስሂን ትምህርት ቤት ስለነበር ወደ ደሴ ሄዱ። ኢንጂነር ጌታቸው በገቡባቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ በትምህርታቸው የላቀ ውጤት ያገኙ ስለነበር በተደጋጋሚ ክፍሎችን እየዘለሉ አልፈዋል።

ወደ አቃቂ ሚሲዮን ገብተው በመማር ላይ እያሉ የሁለተኛ ደረጃ መግቢያ ፈተና ሲመጣ ያለደረጃቸው ፈተናውን ከወሰዱት ተማሪዎች መካከል በእድሜ ትንሹ እሳቸው ነበሩ። ፈተናውን ያልፋሉ ተብሎም አልተጠበቀም ነበር። ኢንጂነር ጌታቸው ፈተናውን አልፋለሁ የሚል ግምት ቢኖራቸውም እኔን ከእነዚህ ትላልቅ ተማሪዎች ጋር ማን አብሮ ይመለከተኛል በማለት ውጤቱ በተነገረበት ዕለት ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር ኳስ እየተጫወቱ ነበር። ፈተናውን ያለፉ ልጆች ሥም ሲጠራ የእሳቸውም ሥም አብሮ ሲጠራ አላመኑም ነበር።



በሳንድስኬፕ አርክቴክት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ

# ምዕራፍ ሁለት
# ወጣትነት በአምቦ የእርሻ ኮሌጅ
# 1938-1944

ኢንጂነር ጌታቸው ከአቃቂ ሚሲዮን ትምህርት ቤት በኋላ በመቀጠል ያመሩት ወደ ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ነበር። ይሄዱና የትምህርት ቤቱን የመግቢያ ፈተና ይወስዳሉ። ፈተናውን በጥሩ ውጤት ያልፋሉ። ፈተናውን ቢያልፉም ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ገብተው ግን አልተማሩም።

"ተግባረዕድ ትምህርት ቤት አትገባም" ይሏቸዋል፤ አባታቸው ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ። "ለምን?" ቢባል "በአሁኑ ጊዜ በአምቦ የእርሻ ኮሌጅ ውስጥ ገብቶ የሚማር ተማሪ በጣም በማፈላለግ ላይ ነን። ለግዜው ኮሌጅ ውስጥ የሚገቡ ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ብዙም ማግኘት አልቻልንም። እናንተ ልጆቼ ደግሞ እዚሁ ቅርቤ እያላችሁልኝ ለምን ልቸገር?" በማለት ስማቸውን ያስመዘግባሉ።

አምቦ የእርሻ ኮሌጅ ተማሪዎችን የሚቀበለው በጊዜው ከባድ የሚባለውን ፈተና ፈትኖ እንጂ እንዲሁ ተማሪ አጣሁ በሚል ማንንም ከየሜዳው አይቀበልም ነበር። ስለዚህም ኢንጂነር ጌታቸው የመግቢያውን ፈተና መውሰድ ነበረባቸው። ወሰዱ። ብዙ ተማሪዎች ነበሩ ፈተናውን የወሰዱት። ፈተናውን ያለፉት ግን በጣም ጥቂቶች ነበሩ። ኢንጂነር ጌታቸውም ፈተናውን ካለፉት ጥቂቶቹ ውስጥ አንዱ ሆኑ። የእርሻ ትምህርታቸውንም በ1938 ጀመሩ።

የአምቦ የእርሻ ትምህርት ቤት የተቋቋመው ጣሊያን ኢትዮጵያን

በ1928 ዓ.ም ከመውረሩ በፊት በብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ (ባላምባራስ ነበሩ)። ጣሊያን ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ ኮሌጁ ሥራውን እንዲቀጥል ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ በአዲስ መልክ መልሰው በሚንስቴር መ/ቤቱ ከነበሩ ሃላፊዎች ጋር በመሆን ትምህርት ቤቱ በኮሌጅ ደረጃ የማስተማር ሥራውን እንዲጀምር መንቀሳቀስ ጀመሩ። በዚህን ጊዜ በመጠኑም ቢሆን ት/ቤቱን ለማስፋፋት ተሞክሯል። እዛው ግቢ ውስጥ በፊት በነበረበት ህንፃ ላይ ነው ኮሌጁ ማስተማሩን የቀጠለው።

ወደ እርሻ ኮሌጅ ለመግባት ተመዝግበው ፈተና ካለፉት ውስጥ ብዙዎቹ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ያልወሰዱ ስለነበሩ፤ ኮሌጁ በአዲስ መልክ በቀረጸው የሁለት ዓመት የመሰናዶ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ ተማሪዎች ገብተው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተደረገ። ሁለቱን ዓመት የመሰናዶ ትምህርታቸውን ተከታትለው ሲጨርሱ ፈተና ይቀመጣሉ። ፈተናውን ያለፉት በእርሻ ኮሌጅ ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ለአራት ዓመት መከታተልና ማለፍ ነበረባቸው። ስለዚህም ኢንጂነር ጌታቸው ሁለት ዓመት መሰናዶ ውስጥ በመቆየታቸው በእርሻ ኮሌጅ ውስጥ የነበራቸው ቆይታ በጠቅላላው 6 ዓመት ነበር።

ኢምፔሪያል ኮሌጅ ኦፍ አግሪካልቸር የሚል መጠሪያ የነበረው የአምቦ አጠቃላይ እርሻ ኮሌጅ የሚሰጠውን ትምህርት ለማስ ቀጠል መጀመሪያ ጊዜ ተማሪዎች ለማግኘት ችግር ገጥሞት ነበር። ስለዚህም ተማሪዎችን ወደ ት/ቤቱ እንዲመጡ ለማማለል የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል። ከዘዴዎቹ ዋነኛው ለተማሪዎቹ ሁለት ሙሉ ልብስና ጫማ በማቅረብ ነበር።





ት/ቤቱ ገና ጀማሪና ያልተሟላ ስለነበር፤ ተማሪዎቹ ምግባቸውን የሚመገቡት በኮሌጁ አቅራቢያ ከሚገኝ ደረጃውን ከጠበቀ ሆቴል ውስጥ ነበር። ቁርስ፣ ምሳና እራት ት/ቤቱ ከተኮናተረው ሆቴል ቤት ሄደው ይመገባሉ። ሂሳቡን ት/ቤቱ ይከፍላል።

በመኝታም በኩል ችግር ነበር። መኝታ ቤት በመጥበቡ የተወሰኑ ተማሪዎች በድንኳን ውስጥ ያድሩ ነበር። ቀስ በቀስ ግን ት/ቤቱ የመመገቢያውንና፣ የመኝታውን ቁሳቁሶች በሟሟላቱ ተማሪዎቹ ከድንኳን ወጥተው ወደ ህንፃው ተዛወሩ፤ ምግባቸውንም በት/ቤት ውስጥ መመገብ ጀመሩ።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ይሰጥ የነበረው ትምህርት በንድፈ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ሆኖ እንደ ሌሎቹ መደበኛ ትምህርቶች ሁሉ መሰረታዊ የሆኑት አማርኛ፣ ሂሳብ፣ እንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ወዘተ ይሰጡ ነበር።

ከሁለተኛ ዓመት ጀምሮ ግን በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ይሰጥ የነበረው ትምህርት በተግባር መደገፍ ጀመረ። ሰፊው ትምህርት እርሻ ነክ በሆኑ ትምህርቶች ላይ ያተኮረ ነበር። ከእርሻው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው የትምህርት ዓይነቶች ቀስ በቀስ እየቀሩ መጡ።

ኢንጂነር ጌታቸው በእርሻ ኮሌጅ ቆይታቸው ስለነበረው የትምህርት ይዘት በአድናቆት የሚያስታውሱት አላቸው፡- “በኮሌጁ ውስጥ እርሻን በተመለከተ ያላጠናነው የትምህርት ዓይነት አልነበረም ማለት እችላለሁ። ትምህርቱ ሁሉን አቀፍ ነበር። ስለ መስኖ ስናጠና ኢንጂነሪንግ እናጠናለን። ትራክተሮችንና ሌሎች የእርሻ መሣሪያዎችን በዝርዝር እንድናውቅ ተደርጓል። በጊዜው በእርሻ ሙያ በዘመናዊ መልክ ብዙ የተማረ ሰው ስላልነበረ፤ አንድ የተማረ

ገበሬ ወደ አንድ አካባቢ ሲላክ የተለያየ ችግር ሲያጋጥመው ከሌላ ሰው የሚጠብቀው ነገር እንዳይኖር በሚል እርሻ ነክ የሆኑ ሁሉን አቀፍ ሙያዎች በኮሌጁ ውስጥ እንዲያውቅና እንዲማር ይደረግ ነበር፡፡ ስለ ፎርስትሪ (ደን ልማት) ይማራል፣ ስለ ከብት እርባታና ህክምና ይማራል፣ በአጠቃላይ በተለያዩ የግብርና ሞያዎች በቂ የሆነ የእርሻ ትምህርት እንዲማር ይደረጋል፡፡”

ትምህርቱ መስጠት እንደተጀመረ፤ በኮሌጁ ውስጥ ከአማርኛ መምህር በስተቀር ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ያስተምሩ የነበሩት የውጭ ሃገር ዜጎች ነበሩ፡፡ መምህራኖቹ ከኢጣሊያ፣ ከስዊዲን፣ ከእንግሊዝ፣ ከሕንድ፣ ከአሜሪካ፣ ከሃንጋሪና ከናይጀሪያ ተመርጠው የተቀጠሩ መምህራኖች እንደነበሩ ነው ተማሪዎቻቸውም ሆኑ የእርሻ ሚንስቴር መ/ቤቱ የሚመሰክሩላቸው፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው በፍቅርና በአክብሮት የሚያስታውሷቸው መምህራን ጥቂት አይደሉም፡፡ “መምህራኖቻችን የምርጥም ምርጥ ነበሩ፡፡ ኢጣሊያዊው ዶክተር ቸሬዛ፣ ናይጀሪያዊው ፕሮፌሰር ያፌስ፣ ኢጣሊያዊው ሲኞር ሮሲ፣ አሜሪካዊው ሚ/ር ሄግንስ ሌሎችም በጥልቀትና በዝርዝር ነበር የሚያስተምሩን.... በሞተር ሜካኒክም ሰባቱን ሲስተሞች ከማወቃችን በተጨማሪ ሞተር ፈተን መጠገን እንችል ነበር፡፡ የአማርኛ መምህራችንም ሊቅ ነበሩ፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ እያጣቀሱ፣ የፊደል አመሠራረትን፣ የግዕዝ አመጣጥን፣ የተለያዩ ሥነ-ጽሑፎችን በስፋት አስተምረውናል፡፡” ይላሉ ኢንጂነር ጌታቸው፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው የአምቦ እርሻ ኮሌጅን የመግቢያ ፈተና እንዳለፉ የገቡት ከመሰናዶው ትምህርት ሁለተኛው ክፍል (ፕሪፓራቶሪ)





ውስጥ ነበር፡፡ 12ኛን ክፍል ጨርሰው የመጡት ተማሪዎች ግን በቀጥታ ኮሌጁ ከሚሰጠው የአራት ዓመት የትምህርት ክፍል ውስጥ ነበር የገቡት፡፡ እኮሌጁ አንደኛ ክፍል የገቡት ተማሪዎች ብዛት ጥቂት ስለነበር መሰናዶው ሁለተኛ ክፍል ካሉት ጎበዝ ተማሪዎች ውስጥ በትምህርታቸውና በፈተናቸው ሻል፣ ሻል ያሉ ተማሪዎችን ወደ ኮሌጁ አንደኛ ክፍል ይዛወሩና ይማሩ ተብሎ በትምህርት አስተዳደሩ ክፍል ይወሰናል፡፡ ስለዚህም ጎበዝ ከሚባሉት ተማሪዎች መካከል አንዱ ኢንጂነር ጌታቸው ነበሩና ወደ ሁለተኛው ክፍል እንዲዛወሩ ተመረጡ፡፡

መጀመሪያ ላይ "እሺ" ይሉና ወደ አንደኛው ኮሌጅ ክፍል ይገባሉ፡፡ አዲሱ ክፍል ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች ሲመለከቱ በትምህርታቸው በጣም ጎበዝና የማትሪክ ፈተናን የወሰዱ ነበሩ፡፡

“ይሄ ነገር ከአቅሜ በላይ ይሆንብኛል” ብለው በማሰብ ወደ መጡበት ክፍል እንዲመልሷቸው የትምህርት ቤቱን ሃላፊ ይጠይቃሉ፡፡ ወንድማቸው ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴ ግን “አይዞህ! ምንም አይቸግ ርህም፡፡ እኛ እናስጠናሃለን” ይሏቸዋል፡፡ ኢንጂነር ጌታቸው ግን “የለም ይቅርብኝ፤ከሥር ከሥሩ ትምህርቴን እያጠናቀቅሁ ብመጣ ይሻላል” የሚል አቋም ስለወሰዱ መምህራኖቹም “አዎን፤ ይሻላል፡፡ ደግሞም ጌታቸው ገና ልጅ ነው” በማለት ወደ ነበሩበት ክፍል መለሷቸው፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው ቀደም ብሎም ቢሆን በትምህርታቸው ከክፍል ክፍል እየዘለሉና እየተዛወሩ የመጡ ተማሪ ስለነበሩ ትምህርቱ አልከበዳቸውም፡፡ በመሠረቱ በክፍል ውስጥ አስተ ማሪው የሚያስተምረውን ትምህርት ሲያስረዳ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጡ፣

መምህሩ ጥቁሩ ሰሌዳ ላይ የሚጽፈውን ጽሑፍ እንዳለ እንደማይ ገለብጡና በፈተናም ወቅት ትምህርቱን እሳቸው በገባቸው መሠረት እንጂ በሸምደዳ አይነት መልስ የማይመልሱ ስለመሆኑ የተረዱ አስተማሪዎች ትምህርቱ የገባው ተማሪ አመላለስ በሚል አበክረው ይናገራሉ። በቀጣይ ህይወታቸውም ይህ ትምህርትን የመከታተል ልዩ ዘዴ ለትምህርታቸውም ለሥራቸውም እንዳገዛቸው ይገልፃሉ።

ኢንጂነር ጌታቸው አስተማሪዎቻቸው የተረዱትን ትምህርት እሳቸው በገባቸው መሠረት በራሳቸው የቋንቋ አጠቃቀም ለፈተናዎች መልስ መስጠታቸውን አስተማሪዎቻቸው ያደንቁላ ቸውና ያበረታቱዋቸው ነበር። "ጌታቸው እኛ መምህራኖች ክፍል ውስጥ ያስተማርናቸውን ትምህርቶች በሚገባ የተረዳ ተማሪ ነው። ስለዚህም ነው በትክክል የተረዳውን ሃሳብ በሸምደዳ መልክ ሳይሆን ወይ ደግሞ ጥቁር ሰሌዳ ላይ መምህሩ የፃፈውን እንዳለ ቃል በቃል ሳይገለብጥ እሱ ባመቸው ቃላትና አረፍተ ነገር በፈተና ላይ መልስ የሚሰጠው። ብዙዎቹ ተማሪዎች ግን የተማሩትን ትምህርት ቢገባቸውም ባይገባቸውም አስተማሪ ዎቻቸው የተጠቀሙባቸውን ቃላትና አረፍተ ነገሮች እንዳለ የፈተና መልሶቻቸው ላይ ይጠቀማሉ" በማለት ኢንጂነር ጌታቸውን በግዜው አበረታተዋቸዋል። በተጨማሪም ኢንጂነር ጌታቸው ከሌሎች መጽሐፍት ያነበቡዋቸውን ትምህርቶቻቸውን በመልሶቻቸው ላይ ስለሚያካትቱ፣ አስተማሪዎቹ እራሳቸው በአጋጣሚ ያላነበቡዋቸውን ትምህርቶች የማወቅ አጋጣሚም ተፈጥሮላቸው ነበር ማለት ይቻላል። ኢንጂነር ጌታቸው በፈተና ውጤታቸው ከክፍላቸው ውስጥ ብዙውን ጊዜ ከአምስት እስከ ሰባተኛ ይወጡ ነበር። በመጨረሻም ከእርሻ ኮሌጅ በአጠቃላይ የእርሻ ሙያ በተመረቁበት ግዜ ከ45 ተማሪዎች 5ኛ ነበር የወጡት። ኢንጂነር





ጌታቸው በነበራቸው ተሰጦ ትምህርት ቤት እያሉ ትምህርት ቤቱን ለማደስ ጨረታ ሲወጣ አብሮ በመጫረት ተደጋጋሚ ጊዜ አሸንፈው ሌሎች ተማሪዎችን ከዛው በመቅጠር ት/ቤቱን ያድሱ ነበር። የኤሌክትሪክ ጀኔሬተሮችንም በኃላፊነት ይጠግኑ ነበር።

በክፍላቸው ከነበሩት ተማሪዎች መካከል ከጎጃም ክፍለ ሃገር ለመጡ ሁለት ተማሪዎች ኢንጂነር ጌታቸው ከፍተኛ አድናቆት ነበራቸው፡ ፡ ተማሪዎቹ ተከታትለው አንደኛና ሁለተኛ ነበር የሚወጡት። እነዚህ ወጣቶች ከአምቦ እርሻ ኮሌጅ በማዕረግ ከተመረቁ በኋላ ወደ አውስትራልያ ተልከው፣ እዛም እሄዱበት በትምህርታቸው ተመስግነውና ተከብረው ነው ወደ ሃገራቸው ኢትዮጵያ የተመለሱት ይላሉ ኢንጂነር ጌታቸው።

የአምቦ እርሻ ኮሌጅ ተማሪዎችን ይቀበል የነበረው ከአንድ አካባቢ ወይም ከአዲስ አበባ ብቻ አልነበረም። በትዕዛዝ ሁሉም ጠቅላይ ግዛቶች የግብርና ሞያ ያለው ምሁር እንዲኖራቸው ከሁሉም ክፍለ ሃገር ነበር ሁለት ሁለት ተማሪዎችን እየመለመሉ ወደ ኮሌጁ የሚያመጡት።

የኮሌጁ ተማሪዎች ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ሥራው ዓለም ከመግባታቸው በፊት በቤተ መንግሥት ሽልማትና ግብዣ ተደርጎላቸው ነበር በሥርዓት የሚመረቁት። ጃንሆይ በየጊዜው ለተለያዩ ሥራዎች አምቦ በሚመጡበት ጊዜ ኮሌጁን ሳይጎበኙና ተማሪዎቹንና መምህራኑን ሳያነጋግሩና ሳያበረታቱ የቀሩበት ጊዜ እንዳልነበር ይነገራል። እነ ኢንጂነር ጌታቸው በ1944 ዓ.ም የተመረቁት ወደ አዲስ አበባ መጥተው በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ነበር።

# ምዕራፍ ሦስት
# ኢንጂነር ጌታቸው በልዩ ልዩ ሥራዎች
# 1946-1947

ኢንጂነር ጌታቸው በአምቦ የእርሻ ኮሌጅ ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ ሲቃረቡ "የእርሻ ሚንስቴር እንደተመረቅን ሥራ ሊሰጠን ወይም እኛን ሥራ ላይ ለመደልደል ጊዜ ይወስድበት ይሆናል" በሚል አርቆ በማሰብ በአባታቸው ቤት ካደገው፤ የአባታቸው ክርስትና ልጅ ከሆነው ከአቦዬ ሃይሌ ጋር በመሆን ከወዲሁ ሥራ ማፈላለግ ጀመሩ። "በሰርቬይንግ ተምረናል ስለዚህ ለአውራ ጎዳና መሥሪያ ቤት የሥራ ጥያቄ ማመልከቻ እናስገባ" ብለው ተመካከሩ። እናም ማመልከቻቸውን ለመሥሪያ ቤቱ አስገቡ። እዛው ትምህርት ቤታቸው እንዳሉም ነበር ለሰርቬይንግ ሥራ (ቅኝት) አውራ ጎዳና እነሱን መቀበሉን ያሳወቃቸው። "መጥታችሁ ሥራ ጀምሩ" ተባሉ።

ወዲያው ከእርሻ ኮሌጁ እንደተመረቁ ቀጥታ በጊዜው ኢምፔሪያል ሃይ ዌይ ኦቶሪቲ ይባል ወደነበረው ወደ አውራ ጎዳና መ/ቤት አመሩ። በዛን ወቅት በዋናነት የመ/ቤቱን ሥራ ያንቀሳቅሱት የነበሩት አሜሪካኖች ነበሩ። በግዜው መ/ቤቱ የባለሙያ እጥረት ስለነበረበት እነ ኢንጂነር ጌታቸውን ወዲያውኑ ነበር ወደ ሥራ ያሰማሯቸው፡ ፡ መጀመሪያ ለቀምት-ስሬ የድልድይ ሥራ ላይ ከአንድ አሜሪካዊ የሥራ ሃላፊ ዳኛው ጋር እንዲሰሩ ተመደቡ።

ቀጥታ ከትምህርት ዓለም ወደ ሥራው ዓለም እንደገቡ ስለቀሰሙት የመጀመሪያ ስለሆነው ተግባራዊ ትምህርት ኢንጂነር ጌታቸው





የሚያስታ ውሱት አብይ ጉዳይ አላቸው "ትምህርት ቤት በነበርንበት ጊዜ ሰርቬይንግ (ቅኝትን) የተለማመድነው ሜዳ ሜዳውን እየፈለግን ነበር። ታዲያ እዛ አዲሱን ሥራ በጀመርኩበት ጊዜ አንድ ቦታ ሰርቬይ እንዲደረግ ሥራ ይሰጠኛል። ቦታው ገደላማ ነበር። መሬቱም ልል ነበር። የቻልኩትን ያህል ሌቭል አደረኩና የትራንዚቱን አስተካክዬ አቁሜያለሁ ብዬ ከአጠገቡ ሄደት አልኩና መለስ ስል ትራንዚቱ ሌቭል ተለውጧል። እንደገና ሞከርኩት፣ አሁንም ተመልሶ ተለወጠ። በርቀት ሥራዬን ይመለከቱ የነበሩት አለቃዬ በቦታው ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጡት አሜሪካዊ "ና ወደዚህ" አሉኝ። እሳቸው ወደ ቆሙበት ቦታ ሄድኩ። "ትምህርት ቤት የት እንደሆነ ታውቃለህ?" ብለው ጠየቁኝና፤ እሳቸው እራሳቸው ለጥያቄው መልሱን ሰጡኝ። "ትምህርት ቤት ያለው እዚህ እሥራ ቦታ ነው" አሉኝ። ከዛም እንዴት ማድረግ እንዳለብኝ አስረዱኝ። ለችካል የሚሆን ሶስት ችካል ቁረጥ፣ ያንን ችካል የትራንዚቱን እግር እምታሳርፍበት ቦታ ላይ አጠንክረህ ቸክል፤ ከዛ ትራንዚቱን እዛ ላይ አቁመው ተባልኩ። እንደተባልኩትም አደረኩ። ሥራውም የተሳካ ሆነ። እንዲህ እንዲህ እየተባለ ሌላውንም እየተማርኩ ሥራው ላይ እየሰለጠንኩበት ሄድኩ ማለት ነው" ብለዋል ሁኔታውን በአንክሮ በማስታወስ።

ከተግባር የሚገኘውን ዕውቀት እየቀሰሙ ከቆዩ በኋላ፤ ሥራቸ ውም በበላዮቻቸው ተቀባይነት ሲያገኝ ለሰርቬይንግ ሥራ ወደ ይርጋዓለም ወንዶ ዲላ የድልድይ ሥራ ቅያስ ተዛወሩ። ይህንን ሥራቸውን አጠናቀው ፈቃድ ላይ እንዳሉ አዲስ አበባ ካለው የአውራ ጎዳና መ/ቤት ቴሌግራም ደረሳቸው። "በአስቸኳይ ትፈለጋለህ" የሚል። የተፈለጉት ለአሰብ-ኮምቦልቻ ሥራ ነበር። ለዚህ ሥራ ብቃት አለው በማለት ስለ እርሳቸው መልካሙን አስተያየት ያቀረቡት አሜሪካዊ

አለቃቸው በእርሻው ኮሌጅ ውስጥ የኢንጂነሪንግ አስተማሪያቸው የነበሩት ሚ/ር ሄግልስ ነበሩ። ኢንጂነር ሄግንስ በዛ አካባቢ ይሰሩ ነበር። እዚህ ቦታ ላይ ሲመደቡ የፕሮጀክቱ ኃላፊ አለቃቸው የነበሩት በኢንጂነሪንግ ከፍተኛ ባለሙያ የነበሩት አሜሪካዊው ሚ/ር ዴቭስ ነበሩ።

አዲሱ ሥራ የ"ወርልድ ባንክ ሳመሪሺት" ማዘጋጀት ነበር። ምን ያህል እንደተሰራ?፣ ምን ያህል ስኩልቨርት?፣ ስንት ድልድይ፣ ምን ያህል አስፋልት እንደተጠናቀቀ ሪፖርት ማቅረብ ነበር። በየወሩ የተሰሩ ሥራዎች ሳመሪ ሺት (ማጠቃለያ) የሚቀናበረው ለሠራተኞች ደሞዝና ለልዩ ልዩ ወጪዎች ክፍያ እንዲያመች ስለተከናወኑ ሥራዎች ለአለም ባንክ ለማሳወቅ ታስቦ ነው። በሥራው ላይ ከተለያዩ ሀገራት የመጡ መሀንዲሶች እንዲሁም ነበሩ። በዋናነት የአርመን፣ የኢጣሊያን፣ የእንግሊዝ፣ የአሜሪካ፣ ወዘተ ዜጎች ነበሩ።

ኢንጂነር ጌታቸው የመጀመሪያ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፣ አሜሪካዊው አለቃቸው የቀረበው ሪፖርት ዝርዝር ነገሮችን በመያዙና የተሟላ ሆኖ ስላገኙት "ገጠር ለገጠር ከመዞርና ከመድከም አዳንከኝ" አሏቸው። ቀደም ብሎ በዚህ የሥራ መደብ ላይ የነበሩት ሠራተኛ ያቀርቡ የነበረው ሪፖርት ውስን ስለነበረና ዝርዝር መረጃ ስላልነበረው የኢንጂነር ሪፖርት አስደሰታቸው። መረጃው የሚሰባሰበው በመኪና እየተዞረ ነበር። በዛን ጊዜ በመኪና መዘዋወሩ ብርቅና አስደሳች እንደነበር ኢንጂነር ጌታቸው በልዩ የደስታ መንፈስ ግዜውን ያስታውሱታል።

የሚሠሩበት አካባቢ በጣም ሞቃት ስለነበረ ለሠራተኞች የሚመች አልነበረም። ኢንጂነር ጌታቸው ለዚህ መፍትሄ ያደረጉት በጠዋት





ቢሮ በመግባት ሥራቸውን አጠናቀው ሲጨርሱ ቢሮ ካለው ጠረጴዛቸው ላይ በግንባራቸው ድፍት ብለው ትንሽ እንቅልፍ እንዲወስዳቸው ማድረግ ነበር። አለቃቸው ደግሞ ትንሽ ሃይለኝነት የነበራቸው ሰው ነበሩና እንዲች ዓይነቷን ድክመት በሠራተኞቹ ላይ ማየት አይፈቅዱም ነበር። የኢንጂነር ጌታቸውን ሥራና ጥንቁቅነት በማየት ግን "ትንሽዬዋን እንቅልፍ" ሰውየው እንዳለዩ ያልፉ ነበር። "ሪፖርቱን በዚህ ቀን፣ በዚህ ሰዓት ታደርሳለህ?" ብለው ይጠይቋቸዋል፤ ሪፖርቱን ተቀብላ የምትወስደውን አውሮፕላን የምትመጣበትን ቀን በማስታወስ። ኢንጂነር ጌታቸውም "አደርሳለሁ" የሚል መልስ ይሰጣሉ። በተባለውም ቀን ሪፖርታቸውን ሠርተው ያስረክባሉ።

አለቅየው ሚ/ር ዴቪስ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ የኢንጂነር ጌታቸው የወር ደሞዝ ሦስት መቶ ብር (300.00) እንዲሆን ሃሳብ አቀረቡ። ይሄ ደግሞ ከአውራ ጎዳና የደሞዝ ጭማሪ ደንብና ሥርዓት ጋር አብሮ የሚሄድ አልነበረም። አውራ ጎዳና ለሠራተኞቹ ደሞዝ ሲጨምር በደንቡ መሠረት ሠራተኛው በሚያገኘው ደሞዝ ላይ ከአንድ አራተኛ በላይ አይጨምርም። ሚ/ር ዴቪስ ግን ተከራክረው የኢንጂነር ጌታቸውን የሥራ ብቃትና ታታሪነት እንዲሁም ሥራው እራሱ የሚጠይቀውን ዋጋ በማስረዳት ደሞዝ እንዲጨመርና ኢንጂነር ጌታቸው የሦስት መቶ ብር ደሞዝተኛ እንዲሆኑ አስደረጉ።

ከዛም ኢንጂነር ጌታቸው ሃገር ሰላም ነው ብለው፣ ዘና ብለው ሥራቸውን እየሠሩ እያሉ ከእርሻ ሚንስቴር አንድ ደብዳቤ ደረሳቸው። "እርሻ ት/ቤት ስትገባ ትምህርትህን ካጠናቀቅህ በኋላ የእርሻ ሚንስቴርን ለአንድ ዓመት ለማገልገል ግዴታ ገብተህ ፈርመሀል፤ ስለዚህ በገባኸው ግዴታ መሠረት ወደ እርሻ ሚንስቴር

እንድትመለስ" ይላል ደብዳቤው። ኢንጂነር ጌታቸው ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም። ስለዚህም ወደ እርሻ ሚንስቴር ተመለሱ።

ወደ እርሻ ሚንስቴር እንደተመለሱ እንደ አጋጣሚ ሆኖ የአሜሪካ ድርጅት የሆነው ፖይንት ፎር ወተር ሪሶርስስ ገና እየተቋቋመ ነበርና የእርሻ ሚኒስቴርን የሚወክል ባለሙያዎች መ/ቤቱ መወከል ስለነበረበት ኢንጂነር ጌታቸው ወደ ፖይንት ፎር ወተር ሪሶርስ ተመደቡ። በድርጅቱ ውስጥም የሃይድሮሎጂ ክፍል ምክትል ሃላፊ ሆነው እንዲሠሩ ተመደቡ። በጊዜው ከተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ባለሙያዎች እየተፈለጉ ወደ ፖይንት ፎር እንዲዛወሩ ተደርጓል። የሰዎች ወደ እዚህ ድርጅት መዛወር ዓላማ ኢትዮጵያዊያኖችን በተለያዩ ሙያዎች ለማሰልጠን ተፈልጎ ነው።

ኢንጂነር ጌታቸው ፖይንት ፎር ወተር ሪሶርስስ ውስጥ ሲሠሩ በነበሩበት ወቅት በኢትዮጵያ ባሉ የተለያዩ ክፍለ ሃገሮች ወንዞች ወዳሉበት የመሄድ ዕድል አግኝተዋል። የቆቃ ግድብና የብሉ ናይል እንዲሁም የሌሎችን ወንዞች የውሃውን መጠን፣ የውሃውን ፍጥነት፣ ውሃው ይዞት የሚሄደውን የአፈር መጠን እንዲሁም ለምን አገልግሎት መዋል እንደሚችል በመመርመር ሥራውን ከሚያጠናው አካል ጋር አብረው ሠርተዋል።

ፖይንት ፎር ወተር ሪሶርስ ውስጥ በመሥራት ላይ ሳሉ ከእርሻ ሚንስቴር አንድ ሌላ ደብዳቤ ደረሳቸው። "ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት ተመልሰህ የሎጅስቲክ ክፍል ምክትል ሃላፊ ሆነህ እንድትሠራ" ይላል ደብዳቤው። ኢንጂነር ጌታቸው ወደ እርሻ ሚንስቴር እንዲመለሱ የተደረገበት ዋናው ምክንያት አሜሪካኖች በኡንራ ስም ለተቋቋመው ድርጅት (UNR) ያስመጧቸውን አዳዲስ ትራክተሮች፣ የመዝሪያ፣





የመከስከሻ፣ ወዘተ መሣሪያዎችን ለማለማመድና ለመቆጣጠር ታስቦ ነው።

እዚሁ ሥራ ላይ እንዳሉ ነበር ወደ ጀርመን ሃገር ሄዶ ለመማር የሚያስችል የነፃ የትምህርት ዕድል (ስኮላርሽፕ) ከጀርመን ሃገር ያገኙት። ስኮላርሽፑን ባገኙበት ወቅት በፖይንት ፎር በኩል አሜሪካ ሄደው ትምህርታቸውን በነፃ ለመቀጠል የሚያስችል ሌላ ስኮላርሽፕ ከአሜሪካ እየጠበቁ ነበር። ይሁንና ከጀርመን የተገኘው ስኮላርሽፕ ስለቀደመ ጉዞው ወደ ጀርመን ሆነ።

# ምዕራፍ አራት
# የትምህርት ቆይታ በጀርመን
# 1647-1951

የኢንጂነር ጌታቸው ፍላጎት ወደ አሜሪካ ሄዶ ትምህርታቸውን መቀጠል ቢሆንም፤ በአጋጣሚ የጀርመኖች የነፃ የትምህርት ዕድል ቀድሞ ስለመጣ ዕድሉ እንዳያመልጣቸው በማለት ከሌሎች ከጀርመን ሃገር የነፃ ትምህርት ዕድል ካገኙት ኢትዮጵያውያኖች ጋር በመሆን ወደ ምዕራብ ጀርመን አቀኑ።

ነፃ የትምህርት ዕድል እንደተገኘ ዝግጅቱ በጣም የተጣደፈ ነበር። በጊዜው አንድ ኢትዮጵያዊ የነፃ የትምህርት ዕድል አግኝቶ ወይም በመንግሥት ለትምህርት ወደ ውጭ ለሚላክ ኢትዮጵያዊ የጉዞውን ጠቅላላ ዝግጅት የሚያከናውነው መንግሥት ነበር።

ሁለት ሙሉ ልብስ (ሱፍ)፣ ካፖርት፣ ጫማና መሀረብ ሳይቀር ለኢትዮጵያውያኖቹ በጣም በተፋጠነ መልኩ ተሰጣቸውና አውሮፕላን ላይ ተሳፈሩ ተባሉ። ነፃ የትምህርት ዕድል ካገኙት መካከል አብዛኞቹ እንኳን ስለ አውሮፕላን ስለ መኪናም የሚያውቁ አልነበረም።

ተማሪዎቹን የጫነው አውሮፕላን ያኔ ወደ ምዕራብ ጀርመን የሚበር የቀጥታ መሥመር ስላልነበረው መጀመሪያ ያረፈው ግብፅ ካይሮ ላይ ነበር።

ካይሮ እንደደረሱ ወደ አንድ ቀደም ብሎ ወደ ተያዘላቸው ሆቴል አመሩ። አዳርም እዛው ሆቴል ውስጥ እንደሚሆን ተነገራቸው። በዛኑ ምሽት የምሽት ክበቦችን ጎበኙ፣ የአረቦችንም እስክስታ ተመለከቱ።





በክበቦቹ ውስጥ ምግቡንም፣ መጠጡንም አዘዙ። መጀመሪያ ላይ ኢትዮጵያዊያኖቹ ለመጠጡና ለምግቡ ስለሚከፈለው ገንዘብ በቂ ትኩረት አልሰጡትም ነበር። ምግቡ ከተበላ፣ መጠጡ ከተጠጣ በኋላ የተጠየቀው ሂሳብ ሲመጣ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ በጣም ተደናገጡ። እንዴት ይከፈል? በጊዜው የነበረው አማራጭ የጠጣውም፣ ያልጠጣውም፣ የበላውም፣ ያልበላውም በጋራ በመሆን ከየኪሶቻቸው አዋጥተው የተጠየቁትን አጠቃላይ ሂሳብ በመክፈል ከውርደትና ከመንገላታት መዳን አለባቸው። ይህንንም ነበር ያደረጉት። ከዛ በመጡበት አውሮፕላን ተሳፍረው ወደ ምዕራብ ጀርመን ሄዱ።

ታውን ፕላነሩና የላንድስኬፕ አርክቴክት ጌታቸው ወደ ጀርመን ሃገር በአውሮፕላን ሲጓዙ ለብሰውት የነበረው ልብስ የሃገር ልብስ ሆኖ፣ ያደረጉት ጫማ ደግሞ ነጠላ ጫማ ነበር። በወቅቱ የጀርመን የአየር ጠባይ በረዷማ ነበር። ጌታቸው ይቺን የአየር ጠባይ ቀደም ብለው አላሰቡበትም። የታያቸው የሃገራቸው የባህል ልብስ ምን እንደሚመስል ማሳየቱ ላይ ነበር። የለበሱትን ልብስ በሌላ ልብስ ለመቀየር አልቻሉም። ሱፍ ልብሶቻቸው ሻንጣዎቻቸው ውስጥ ተቆልፎባቸዋል። ሻንጣው ያለው ደግሞ የአውሮፕላኑ የዕቃ መጫኛ ውስጥ ነበር። ስለዚህ ሻንጣቸው ከአውሮፕላኑ ላይ እስኪወርድ ድረስ የእንግዳ መቀበያ ውስጥ ተቀምጠው መጠበቅ ነበረባቸው። በመጨረሻም ሻንጣው መጣላቸው፣ ልብሳቸውንም፣ ጫማቸውንም ቀይረው ከአውሮፕላን ማረፊያው ለመውጣት ቻሉ።

ኢንጂነር ጌታቸው አስተዳደጋቸው የአውሮፓን ሁኔታ የሚያውቅ ቤተሰብ ውስጥ ስለነበር አውሮፓ ሲገቡ የጎላ መደነጋገር አልደረሰባቸውም። አብረዋቸው ወደ አውሮፓ ተጉዘው የነበሩት ሌሎች ኢትዮጵያውያኖች ግን መጠነኛ የሆነ ጊዜያዊ ግራ

መጋባት ገጥሟቸው ነበር። በተለይ የሚበሉትን ምግብ ማዘዝ ላይ፣ የማያውቁትና ያልለመዱት እየሆነባቸው ለተወሰነ ጊዜ ትንሽ ተቸግረው ነበር።



በጀርመን የሚገኝ ትልቁ ጀርመንያ ሐውልት

ኢትዮጵያውያኖቹን ተማሪዎች ጀርመን ውስጥ የተቀበላቸው





የጀርመን ቋንቋ የማስተማሪያ ተቋም የሆነው ገተ ኢንስቲቲዩት ነበር። ተቋሙ ተማሪዎቹን መጀመሪያ ወደ ሙኒክ ከተማ ከዛ በትራሂልሃል ወደ እምትባል መንደር ወሰዷቸው። በዚች በትራሂልሃል በምትባል መንደር ውስጥ ነበር፣ የጀርመን ቋንቋንና በጀርመን ውስጥ ለመንቀሳቀስና ለመኖር የሚያስችላቸውን ክህሎት እንዲቀስሙ የተደረጉት።

ለሶስት ወር ያህል የጀርመንኛ ቋንቋና ሌሎች ዕውቀቶችን እንዲያገኙ ከተደረገ በኋላ ኢትዮጵያዊያኖቹ በሚያጠኑት የትምህርት ዓይነት በየተቋሙና በየዩኒቨርስቲው ተደለደሉ። ሃምቡርግ የሄደ አለ፣ ሌላው ቪስባደን፣ ሌላው ደግሞ ሃኖቨር፣ ወዘተ እያለ በየቦታው ተበታተኑ።

ኢንጂነር ጌታቸው ያመሩት በራይንላንድ ውስጥ ወደ ምትገኘው ጋይዘንሃይም ነበር። በጋይዘንሃይም ከፍተኛ የትምህርትና የምርምር ኢንስቲቲዩት ሲሆን ከተማዋ በስፋት የኢንስቲቲዩቱ ይዞታ ነው። ወደ እዚህ ኢንስቲቲዩት የሚመጡት ተማሪዎች አብዛኞቹ የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን ለመከታተል ነው። በአብዛኛው የሚመጡትም ከአሜሪካ፣ ከእንግሊዝ፣ ከኢጣሊያ ወዘተ ነው። በዛን ወቅት በዛ ትምህርት ቤት ውስጥ ለከፍተኛ ትምህርት ሁለት የጥቁር ዜግነት ካላቸው ተማሪዎች አንዱ ኢንጂነር ጌታቸው ሆነው ተገኙ።

ከሁለት ዓመት ቀደም ብሎ ግን በዚህ ኢንስቲቲዩት ውስጥ ሁለት ኢትዮጵያውያኖች እየተማሩ ነበር። እነዚህ ኢትዮጵያውያኖች በዚህ ተቋም ውስጥ ያጠኑት ባጠቃላይ ስለ ፍራፍሬ ሆኖ ጥናቱ በወይን አጠማመቅ ላይ ያተኩራል። ትምህርቱ ከንድፈ ሃሳብ ይልቅ ወደ ተግባራዊ ትምህርት ያደላል።



ኢንጂነር ጌታቸው በጀርመን ትምህርት ቆይታቸው ከተማሪዎች ጋር

ኢንስቲቲዩቱ የሚሰጣቸውን ተግባራዊ ትምህርት ለማስተማር የተሟላ በቂ ማቴሪያልና ከፍተኛ ብቃት ያላቸው ሳይንቲስቶች መምህራን አሉት። በእንዲህ ዓይነቱ መሠረታዊ የትምህርት መስክ የማይሳተፉ ተማሪዎች መንግሥት በሚያዘጋጀው ብሔራዊ ፈተና ላይ አይሳተፉም። ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ፣ የሚሰጣቸው የትምህርት ማረጋገጫ ማይስተር ሰርተፊኬት ይባላል (ለተማሪው የሥራ ልምድ ባለቤት ማለት ነው)። ስለ እነዚህ ተማሪዎች ኢንጂነር ጌታቸው ሲናገሩ “ተማሪዎቹ በትምህርታቸውና በሥራቸው ኩራት ይሰማቸዋል። ሲማሩም ጥርት አድርገው ነው” በማለት ይመሰክሩላቸዋል።





እነዚህ ኢትዮጵያውያኖች የእነሱን ሙያ እንዲያጠኑ ኢንጂነር ጌታቸውን ጠይቀዋቸው ነበር። ይሁንና ኢንጂነር ጌታቸው በወተር ሪሶርስ የነበራቸው ቆይታ ወደ እዚህ ሙያ እንዲያዘነብሉ አልገፋፋቸውም። የእሳቸው ምርጫ ታውን ፕላኒንግና ላንድስኬፕ አርክቴክቸር ሆነ።

ኢንጂነር ጌታቸው መማር የሚፈልጉትን ሙያ ለኢንስቲቲዩቱ ባሳወቁ ጊዜ ኢንስቲቲዩቱ ወዲያውኑ አልተቀበላቸውም። “አንተ የተማርክበትን ካሪኩለም ስለማናውቅ፤ ይህን ሙያ ለማጥናት ምርጫህ ከሆነ ለፈተና መቅረብ አለብህ” ይላቸዋል። እሳቸውም ምንም ሳያቅማሙ ለፈተናው ለመቀመጥ ዝግጁነታቸውን ገለጹ።

በመሠረቱ ጀርመኖች አንድ እራሱን የቻለ የጠበቀ ህግ አላቸው፡ ፡ አንድ ጀርመናዊ የሆነ የእነሱ ተማሪ ለከፍተኛ ትምህርት የሚያበቃውን የፈተና ውጤት ካመጣ በኋላ ተጨማሪ ትምህርት ለመማር ከጠየቀ በቅድሚያ ለሁለት ዓመት ያህል ተግባራዊ በሆኑ ሥራዎች ላይ መሳተፍ ግድ ነው።

ጀርመኖች መጀመሪያ የኢንጂነር ጌታቸውን የትምህርት ደረጃ ለማወቅ ወደ አዲስ አበባ ጽፈው ጠየቁ፣ ከዛ ቀጠሉና ኢንጂነር ጌታቸውን ለፈተና አስቀመጧቸው። በኬምስትሪ፣ በፊዚክስ፣ በሂሳብና በባዮሎጂ እንዲፈተኑ ተደረገ። እሳቸውም ከአዲስ አበባ ቀደም ብለው እንዲላኩላቸው የጠየቋቸውን መጽሐፍት በማምጣት ቀደም ብለው በተማሩት ላይ ክለሳ ካደረጉ በኋላ ፈተናውን ወሰዱ። ፈተናውን አለፉ።

ጀርመኖች ሥራ ላይ በጣም ዲስፕሊንድ የሆኑ በመሆናቸው ኢንጂነሩ ከእነሱ እጅግ በጣም ብዙ ነገሮችን እንደተማሩና ካላቸው ጠንካራ

የተፈጥሮ አስተያየት ጋር በማዋሃዳቸው ለቀጣዩ ሥራዎቻቸው ሁሉ አብይ አስተዋፅኦ እንዳደረጉላቸው ኢንጂነር ጌታቸው በአጽንኦት ይናገራሉ፡፡

"በዛን ጊዜ ጀርመኖች ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተላቀው በኢኮኖሚያቸው ገና ያላገገሙ ስለነበር የሚኩራሩበት ኑሮ አልመሠረቱም ነበር፡፡ አንድ ሰው ኮንዶሚኒየም ካለው እሱ ከክፍሎቹ ውስጥ በጣም ጠባብዋ ክፍል ውስጥ እየኖረ ቀሪውን ክፍሎች ያከራያል፡፡ በመሠረቱ ደህና የወር ገቢ አላቸው የሚባሉት እንኳን በተጨናነቀ ሁኔታ ነበር የሚኖሩት፡፡ ዩኒቨርስቲው ዶርሚተሪ ስለሌለው እኛም በሚሰጠን ገንዘብ ከግለሰቦች ቤት ተከራይተን ነበር የምንኖረው፡፡ ምግባችንንም ቤት አከራዮቻችን ነበር የሚያበስሉልን፡፡" ብለዋል ስለ ነበረው ሁኔታ እያስታወሱ፡፡

ጀርመኖች በቀለም ልዩነት የሚያምኑ ናቸው ተብለው ቢታሙም ኢንጂነር ጌታቸው ግን አለ የሚባለው የዘር አድልዎ አልደረሰባቸውም፡፡ እንደውም ለኢትዮጵያውያኖች የሚሰጡት ክብር የላቀ እንደነበረ ነው ኢንጂነር ጌታቸው የሚናገሩት፡፡

በጀርመን የትምህርት ሥርዓት አንድ ተማሪ ትምህርቱን አጠናቆ ጨርሷል የሚባለው በዛ በተማረበት ሙያ የሚቀርብለትን የቃልና የጽሑፍ ፈተና ካለፈ ነው፡፡ ኢንጂነር ጌታቸውም ለፈተና ሲቀርቡ የጽሑፉም፣ የቃልም ፈተና ቀርቦላቸው ከጽሑፍ ፈተናው ይልቅ በቃል ፈተናው የተሻለ ውጤት አመጡ፡፡ ለአገኙት ጥሩ ውጤትም የቃል ፈተናው በእጅጉ እንዳገዛቸው ይናገራሉ፡፡

በላንድስኬፕ አርክቴክትነትና በታውን ፕላኒንግ የባችለር ድግሪያቸውን እንዳገኙ ዩኒቨርስቲው ወደ ኢትዮጵያ አንድ ጽሑፍ ይጽፋል፡





፡ የተላከው ደብዳቤ ኢንጂነር ጌታቸው ወደ ሃኑቨር ዩኒቨርስቲ ሄደው ትምህርታቸውን በዶክትሬት ደረጃ እንዲቀጥሉ የኢትዮጵያን መንግሥት የሚጠይቅ ነበር፡፡


የኢትዮጵያ፡ንጉሠ፡ነገሥት፡መንግሥት፡
የርሻ፡ሚኒስቴር፡

መንግሥትም ኢንጂነር ጌታቸውን ትምህርታቸውን ለመቀጠል ያላቸውን ፈቃደኝነትና የሚያስፈልጋቸውን ወጪዎች በአስቸኳይ እንዲያቀርቡ ጠየቃቸው፡፡ ኢንጂነር ጌታቸው ግን መጀመሪያ ለተወሰነ ዓመትም ቢሆን በተማሩት ትምህርት ሃገራቸውን ለማገልገል ስለወሰኑ ወደ ኢትዮጵያ መመለሱን እንደሚመርጡ አስታወቁ፡፡ ስለዚህም

እንደተመረቁ ቀጥታ ወዲያም ወዲህ ሳይሉ ወደ ሃገራቸው ተመለሱ።

ከጀርመን እንደተመለሱ ጃንሆይ ዘንድ ቀርበው ነበር። በጊዜው ከውጭ ተምሮ የሚመጣ ኢትዮጵያዊ ጃንሆይ ዘንድ ቀርቦ ተመክሮና ተመርቆ ነበር ወደ ሥራው ዓለም የሚሠማራው።

በመሠረቱ አንድ ኢትዮጵያዊ ለትምህርት ወደ ውጭ ሃገር ሲላክም ሆነ ሲመለስ ጃንሆይ ዘንድ መቅረብ ግድ ነበር። ለዚህ ዋናው ምክንያት በጊዜው ጃንሆይ የትምህርት ሚንስቴር ሚንስተር እሳቸው እራሳቸው ስለነበሩ ነው።





# ምዕራፍ አምስት

## አፍሪካ አዳራሽና አርክቴክት ጌታቸው

ኢንጂነር ጌታቸውን ለትምህርት ወደ ምዕራብ ጀርመን የላካቸው የእርሻ ሚንስቴር መ/ቤት ቢሆንም በጀርመን ቆይታቸው ያጠኑት ሙያ "ታውን ፕላኒንግና ላንድስኬፕ አርክቴክቸር" በመሆኑ ሙያቸው ሊያሠራቸው ወደ እሚያስችላቸው ተቋም አመሩ - ወደ አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት። ለማዘጋጃ ቤቱ የሥራ ቅጥር ማመልከቻቸውን አቀረቡ። ማዘጋጃ ቤቱ ማመልከቻቸውን በመቀበል ወዲያውኑ ሥራቸውን እንዲጀምሩ አደረገ።

በጊዜው ለትምህርት ከውጭ ሃገራት ቆይተው ወደ ሃገራቸው ከተመለሱና በየሥራ ዘርፉ ከቀጣሪው መ/ቤት ከተደራደሩ በኋላ ቀጣሪው ከጽህፈት ሚንስቴር መ/ቤት የሥራ ቅጥር ማዘዣ ለሚመለከተው ቀጣሪ አካል የሚጻፈው። አካሄዱን "ከፈረሱ በፊት ጋሪው" የሚል ዓይነት ቢያስመስለውም የኢንጂነር ጌታ ቸው በማዘጋጃ ቤት የመቀጠር ሂደትም ተመሳሳይ ነበር። ሥራ ከጀመሩ በኋላ ነበር ጽህፈት ሚንስቴር ለማዘጋጃ ቤት የቅጥር ደብዳቤ የጻፈላቸው።

በአዲሱ ሙያቸው በመጀመሪያ እንዲሠሩ የተመደቡት በማ ዘጋጃ ቤት ውስጥ "ፓርክና መናፈሻ" በሚባል ክፍል ውስጥ ነበር። ይህንን ክፍልና ሌሎችንም ጨምሮ በግዜው በሃላፊነት የሚመሩት ኢጣሊያዊው ኢንጂነር ኮሎምቦ ነበሩ። ሰውዬው በሙያቸውና በታታሪነታቸው ምስጉን እንደነበሩ ይነገርላቸዋል። ኢንጂነር

ጌታቸው እዚህ ክፍል ውስጥ ሲመደቡ ያላቸው ሙያ ብቁ ስለነበር ክፍሉ እራሱን ችሎ እንዲሠራ ተደረገ።

ኢንጂነር ጌታቸው ሥራቸውን በጀመሩበት ወቅት የአፍሪካ መሪዎች ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ ተብሎ የሚጠበቅበት ወቅት ስለነበር አዲስ አበባ ከፍተኛ የሥራ ውጥረት ውስጥ ነበረች። የሕንፃ ግንባታው መንገዱ፣ መብራቱ፣ ፅዳቱ፣ ሁሉም። በተለይ በመንገዱ ላይ አዲስ የሚተከሉ አትክልቶችም ሆነ የነበሩትን የማስተካከል ሂደት ከፍተኛ ትኩረት ያገኘበት ጊዜ ነበር።

በቤተ መንግሥቱና ገና ጥናቱ በመጠናቀቅ ላይ ያለው የአፍሪካ አዳራሽ ሕንፃ አካባቢ ያለው ቦታ በጣም የተጎሳቆለና ጽዳት የጎደለው ነበር። ይህንን ቦታ ጽዱና ያማረ ለማድረግ ቀደም ብሎ በኢንጂነር ኮሎምቦና ረዳታቸው የተዘጋጀ ፕሮጀክት ነበር። ይህንን ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ ነበር ኢንጂነር ጌታቸው የተፈለጉት። ዕቅዱ ዋናው መሀንዲስ ኮሎምቦና ረዳቱ ጂኦሜትራ ዳሩኛ ከሥር ከሥር ጥናቱን እያጠኑ፤ ያጠኑትን ዝርዝር ጥናት ለኢንጂነር ጌታቸው በማስተላለፍ ሥራው እንዲሠራ ነበር።

ኢንጂነር ጌታቸው ይቺን አካሄድ አልተቀበልዋትም። በመጀመሪያ ስለ አጠቃላይ ፕሮጀክቱ ለመረዳት የተዘጋጀው ፕሮጀክት እንዲሰጣቸው ጠየቁ። ይህ እሳቸው የጠየቁት ፕሮጀክት ደግሞ ለጃንሆይ ቀርቦ ሊጸድቅ ጥቂት ቀናት ብቻ ነበር የቀሩት። ኢንጂነር ጌታቸው ደግሞ ፕሮጀክቱን ሲመለከቱት ዕቅዱ ከብዙ አቅጣጫ ብቁ ሆኖ አላገኙትም።

ስለዚህ በጊዜው የአዲስ አበባ ከንቲባ ለነበሩት ለከንቲባ ዘውዴ ገ/ሥላሴ "ይሄ ፕሮጀክት" ይላሉ፣ "ይሄ ነገር እኮ ልክ አይደለም ። አንደኛ ነገር የግንብ ብዛት አለው። ሁለተኛ ከፍተኛ ወጪ






ይጠይቃል። ሦስተኛ ለመኪና ማቆሚያ የተከለለው ቦታ 250 መኪና ብቻ ማስተናገድ እንዲቻል ተደርጎ ነው የታሰበው። ይህንን ቦታ ከዛ በተሻለና ዘመናዊ በሆነ መልክ በመገንባት ለብዙ መኪናዎች ማቆሚያ ጭምር ማድረግ ይቻላል። በጣም ተዳፋት ያለው ቦታ ከሆነ ደግሞ የሚሠራው ሥራ ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። ስለዚህ "እኔ ላጥናው" በማለት ይጠይቃሉ።

ከንቲባው የጊዜው መቃረብ ያሳስባቸውና "ጊዜ የለንም፣ ይሄ ጥናት እራሱ ብዙ ጊዜ ፈጅቷል። በፕሮጀክቱ መሠረት ቶሎ ተብሎ ወደ ተግባር መግባት ይኖርብናል" ይላሉ።

ኢንጂነር ጌታቸው ግን በሃሳባቸው በመጽናት "እኔ ሌትና ቀንም ቢሆን ሠርቼ በቶሎ አደርሳለሁ፤ ትንሽ ቀን ብቻ ይስጡኝ" ይሏቸዋል። ከንቲባው የኢንጂነር ጌታቸውን ሁኔታና ለፕሮጀክቱ የሰጡትን ከፍተኛ ትኩረት በማስተዋል "እስቲ ይሁን" በማለት አጭር መልስ ሰጥተው ጥያቄያቸውን ተቀበልዋቸው።

ኢንጂነር ጌታቸው በገቡት ቃል መሠረት ቀንና ሌሊት በመስራት በጥቂት ቀናት ውስጥ ንድፉን ሠርተው ለከንቲባው አቀረቡ። ከንቲባው የቀረበላቸውን ንድፍ ሲመለከቱ፣ በንድፉ በእጅጉ ተሳቡ። ንድፉን ሲመለከቱት ለ250 መኪና ማቆሚያ ታስቦ የነበረው ቦታ ወደ 525 መኪና ለማስቆም መቻሉን ተገነዘቡ። በዛ ላይ በበፊቱ ፕሮጀክት ላይ እነዛ የተንዛዙና አላስፈላጊ ግንቦች ቀርተው ሁሉ ነገር መልክ መያዙን በመረዳት ክቡር ከንቲባው በኢንጂነር ጌታቸው በቀረበው ንድፍ ይደሰቱና "እንዲህማ ከሆነ ቶሎ ጨርሰው" ይልዋቸዋል። ኢንጂነር ጌታቸውም ፕሮጀክታቸውን በጥንቃቄና በፍጥነት በመጨረስ ለከንቲባው አቀረቡ።




ይህ ጥናት ለኢንጂነሪንግ ኮሚቴ ለመቅረብ ምንም ጊዜ አልፈጀ





በትም:: ጥናቱ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ለኮሚቴ ቀረበ:: የኮሚቴው ሰብሳቢ የነበሩት ፈረንሳዊ የምህንድስናው ክፍል ዋናው መሐንዲስ ነበሩ:: ኢንጂነሩ ቀደም ብሎ በእነ ኢንጂነር ኮሎምቦ ተጠንቶ የነበረውን ፕሮጀክት ያውቁታል::

በዚህ ስብሰባ ላይ የበፊቱን ፕሮጀክት ያሰናዱት ኢንጂነር ኮሎምቦና እረዳታቸው ጂኦሜትራ ዳሩኛ ተገኝተዋል:: ስብሰባው ሲጀመር ኢንጂነር ጌታቸው አዲስ ስለ አዘጋጁት ፕሮጀክት እንዲያስረዱ ተጠየቁ:: እሳቸውም በጥንቃቄና በእርጋታ ስለ ቀረጹት ፕሮጀክት በዝርዝር ለተሰበሰበው ኮሚቴ አስረዱ:: የቦታውን ስፋትና ጥበት፣ ቦታዎች ለምን ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ፣ የገንዘቡን ወጪ፣ የዛፎቹንና የዕፅዋቶቹን ዓይነት፣ ቁመታቸውን፣ ዕይታ የማይከለክሉ ስለመሆናቸው፣ በአጠቃላይ ስለሚኖራቸው የውበት ገፅታ በዝርዝር አሳወቁ::

የኢንጂነር ጌታቸው ገለፃ እንዳበቃ ፕሮጀክቱን አስመልክቶ ጥያቄዎች መቅረብ ጀመሩ:: ፈረንሳዊው መሀንዲስ የኢንጂነር ጌታቸው ገለፃ የኢንጂነር ኮሎምቦን ክብር የሚነካ መስሎ ስለተሰማቸው ለኮሎምቦ ጥብቅና የመቆም አዝማሚያ አሳዩ:: ለማጥላላትም የተለያዩ ግን አላስፈላጊ ጥያቄዎችንም ለኢንጂነር ጌታቸው አቀረቡላቸው:: ኢንጂነሩ አጥጋቢ የሆኑ መልሶችን ሰጡ::

በመጨረሻም ከቦታው ተዳፋት ጋር በማያያዝ "ፍሬን የሌለው መኪና የሆነስ እንደሆነ?" የሚል ጥያቄ በፈረንሳዊው ዋና መሀንዲስ ለኢንጂነር ጌታቸው ቀረበላቸው::

"እሱማ እንዴት ይሆናል?" አሉ ኢንጂነር ጌታቸው:: "በመጀመሪያ ደረጃ ፍሬን የሌለው መኪና እንዲሽከረከር አይፈቀድም" አሉ:: የተጀመረው ምልልስ አላዋቂ ሊአደርጋቸው እንደሚችል በነገሩ ቶሎ የነቁት ኢንጂነር

ኮሎምቦ፣ የኢንጂነር ጌታቸው አካሄ ድና አመላለስ ፈረንሳዊውን ዋና መሀንዲስ አጣብቂኝ ውስጥ ሊከታቸው ይችላል ብለው በመፍራት ፈጥነው "አርክቴክት ጌታቸው ያቀረበው ጥናት የተሻለ ነው። ስለዚህ ፕሮጀክቱ ቶሎ ብሎ ተግባራዊ ቢሆን ይመረጣል" የሚል እጥር ምጥን ያለ ሃሳብ በማቅረብ፤ ኢንጂነር ኮሎምቦ ስብሰባው እንዲዘጋ አደረጉ፡ ፡ የኢንጂነር ጌታቸው ፕሮጀክትም በሙሉ ድምፅ ተቀባይነት አገኘ።

የኮሚቴው አባላትም፡-

1. ዋናው መሐንዲስ ሰብሳቢ
2. አርኪቴክት ለማርሻ የሕንፃ ጥናቶች ኃላፊ
3. ኢንጂነር ኮሎምቦ ከነረዳታቸው
4. ኢንጂነር ከበደ አካለወልድ የመንገድ ክፍል ም/ኃላፊና እኔም ጌታቸው ማኀተመሥላሴ ነበርን።

ተቀባይነት ያገኘው ፕሮጀክት ዝርዝር ሂሳብ እንዲወጣለት ተደረገ። ዝርዝር ሂሳቡም በራሳቸው በኢንጂነር ጌታቸውና በኢንጂነር ከበደ አካለወልድ እንዲዘጋጅ ሆነ። እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ጥናቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማስፈቀድ የተሟላው ጥናት በኢንጂነር ጌታቸው አስረጅነት በከንቲባው አማካኝነት ለጃንሆይ ቀረበ። ጃንሆይም ፕሮጀክቱ ሥራ ላይ እንዲውል ፈቀዱ።

ፕሮጀክቱ በጃንሆይ ከተፈቀደ በኋላ ለጨረታ እንዲቀርብ ተደረገ። ጨረታውን አንድ ኢጣሊያዊ ኮንትራክተር (የሥራ ተቋራጭ) አሸነፈ፡ ፡ የሥራው ተቆጣጣሪ መሀንዲስም ፕሮጀክቱን ያሰናዱት ኢንጂነር ጌታቸው እንዲሆኑ ተወሰነ። በመሠረቱ ጥናቱን ያጠኑት እሳቸው በመሆናቸውና ሥራውም የሚመለከተው የእሳቸውን ክፍል ስለሆነ ተቆጣጣሪነቱ የእሳቸው የራሳቸው ከመሆን አይዘልም ነበር።

ሥራው ተጀመረ። ኢንጂነር ጌታቸው ስራው በፕሮጀክቱ ውጥን ላይ





በተደረገው ስምምነት መሠረት ተግባራዊ መሆኑን መከታተላቸውን ቀጠሉ። ሠራተኞች የዕለት ሥራቸውን አጠናቀው ሲሄዱ፣ ኢንጂነር ጌታቸው በዕለቱ የተሠራውን ሥራ በዝርዝር እየዞሩ ይመለከታሉ። በትክክል ያልተሠራ የመሰላቸውን እንደገና እንዲሠራ ያደርጋሉ።

በዛኑ ሰሞን የኢንጂነር ጌታቸው ማኀተመሥላሴን አሻራ በታሪክ ያስመዘገበ አንድ አብይ ጉዳይም ተፈጽሟል። አሻራው የአፍሪካ አዳራሽ ሕንፃን አቀማመጥ የሚመለከት ነው።የአፍሪካ አዳራሽ ህንፃ ፕላን ተገምግሞ በሚመረጥበት ጊዜ የአፍሪካ አዳራሽ ፕላን አሁን ያለውን አቀማመጥ የያዘው ኢንጂነር ጌታቸው ባቀረቡት ወሳኝ ሃሳብ ስለመሆኑ ታሪክ የሚመሰክረው ሃቅ ነው።

የኢንጂነር ጌታቸው ሃሳብ ከመቅረቡ በፊት የህንፃው የአቀማመጥ ፕላን ገጽታ ፊቱ ወደ ሂልተን ሆቴል ተደርጎ ነበር የቀረበው።

በጊዜው በማዘጋጃ ቤት ሳይት ፕላነር አልነበረም። ኢንጂነሩም፣ ሰርቬየሩም፣ ጂኦሜትራውም ሁለ ገብ ሆነው ነበር ሥራቸውን የሚሠሩት። ስለዚህ ውበትንና ምቾትን ያካተተ ሥራ መሥራት አልተቻላቸውም። "ሁሉም በሞያቸው ላይ ብቻ ነው ያተኮሩት"።

የአፍሪካ አዳራሽን ፕላን በተመለከተ ወደ ማጠቃለያው ውሳኔ ላይ ለመድረስ ስለ ፕሮጀክቱ አጠቃላይ ስብሰባ እንዲደረግ ተወሰነ። በዚህ ስብሰባ ላይ ኢንጂነር ጌታቸው እንዲገኙ በአርክቴክት ለማርሻ አማካይነት ተጋበዙ። የተጋበዙት በሳይት ፕላነርነት ደረጃ ነበር። በዚህ ስብሰባ ላይ የተገኙት ባለሙያዎች የረዥም ጊዜ የሥራ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ሲሆኑ፤ ኢንጂነር ጌታቸው ብቻ ነበሩ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት።

በህንፃው አጠቃላይ ገጽታ ላይ ሰፋ ያለ ውይይትና ምክክሩ ሲጧጧፍ፣ በህንፃው አቀማመጥ ላይ ኢንጂነር ጌታቸው የሆነ ስህተት ተመለከቱ።

ተሰብሳቢው አንድ ዓይነት ስምምነት ላይ በመድረስ ውሳኔውን ሊያሳልፍ ሲል፤ ኢንጂነር ለተሰብሳቢው አስተያየት ለመስጠት እንደሚፈልጉ አሳወቁ፡፡

ተሰብሳቢው ግራ በመጋባት ፊቱን ወደ አርክቴክት ጌታቸው አዞረ፡፡ ኢንጂነር ቀጥታ ወዳ ታያቸው ስህተት አመሩ፡፡ "ይሄ ሕንፃ አቀማመጡ ልክ አይደለም፡፡ የህንፃው ፊት በዋናው መንገድ በኩል መሆን ሲገባው እንደዛ አይደለም የሆነው፡፡ በዋናው መንገድ ላይ የሚሄድ ሰው የህንፃውን ውበት ሊያየው ይገባል፡፡ የሆነው ግን ጠባቡ ክፍል ወደ ዋናው መንገድ፣ ሰፊው ገጽታና የህንፃው ዋናው ውበት ደግሞ ወደ ተሸፈነው ሂልተን ሆቴል አቅጣጫ ሆኗል፡፡ ሰፊ ጀርባው ያለው ደግሞ ወደ እስጢፋኖስ ነው የተደረገው፡፡ ይሄ ልክ አይደለም" ካሉ በኋላ በመቀጠል "ጠባቡን ክፍል ወደ ምሥራቅ፣ ሌላውን ጠባቡን ክፍል ደግሞ ወደ ምዕራብ ነው ያደረጋችሁት፡፡ ሰፊው ክፍል ግን ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ ነው የተደረገው፡፡" ሕንፃው በዚህ መልክ ቢሠራ ሕንፃው ውበቱን ከማጣቱ በላይ ሕንፃው የምስራቅንና የምዕራብን ፀሐይ ሙቀት አሙቱን ሙሉ ስለማያገኙ በማቀዝቀዣ ውስጥ ሁነው እንዲሰሩ እንደ መፍረድ ይቆጠራል ሲሉ ፕሮጀክቱን የሠሩት አርክቴክት ሙሴ ዶሚኖ በቀረበው ሃሳብ ላይ ምንም ክርክር አላነሱም፡፡ "አርክቴክት ጌታቸው ያቀረቡት ሃሳብ ትክክል ነው፡፡ አስተካክዬ አቀርባለሁ" በማለት አርክቴክት ሜዜዲሚ ቃል ገባ፡፡

አርክቴክቱ እንዳሉትም በአርክቴክት ጌታቸው ሃሳብ መሠረት አስተካክለው አቀረቡ፡፡ ከዛም በላይ ከፊት ለፊቱ ላይ በግራ በቀኝ መውጫና መውረጃ እንዲሁም ፋውንቴን አክለውበት አሳ መሩት፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮ የኢንጂነር ጌታቸው ማህተመሥላሴ የሙያ ምክር እጅግ ተፈላጊ እየሆነ መጣ፡፡





# ምዕራፍ ሥድስት

## በጽዳትና ንባን ክፍል

ኢንጂነር ጌታቸው በመቀጠል የመናፈሻ፣ የመዝናኛና እንዲሁም ጽዳትና ጤና ጥበቃውን አብረው እንዲሰሩ በተደረገበት ወቅት በክፍሉ ውስጥ ብዙ መሻሻሎች ለማድረግ ሞክረዋል፡፡

ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በአዲስ አበባ የሚታየው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ እሳቸው የክፍሉ ኃላፊ ሆነው በሚሰሩበት ግዜ የመጣ ነው፡፡ መክደኛም ነበረው፡፡ ይህ በሃይድሮሊክ የሚያነሳ የቆሻሻ ማጓጓዣ በማስፈለጉም መርሰዲስ መኪናዎችን ያስመጡ ከነበሩት ከሚስተር ላምበርት ጋር በመወያየትና በማግባባት መኪናዎቹን ከነገንዳው በዱቤ እንዲገዛ ስለተስማማን ምክር ቤቱም እንዲገዙ ስለፈቀደ ተገዝተው ሥራ ላይ ዋሉ፡፡

ጽዳቱን በማስጠበቅ በኩል የወጡትን ደንቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ከደንቦቹ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ "ማዘጋጃ ቤቱ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎችን በየቦታው ለአካባቢው ሕዝብ ሲያስቀምጥ ተገልጋዩ ሕዝብ ደግሞ በበኩሉ በአጥር ግቢው ውስጥ ክዳን ያለው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃ (በርሜል) እንዲያስቀምጥ፣ ወደ ቆሻሻ ገንዳ በሚገለበጥበት ጊዜ ደግሞ ገንዳው አለመሙላቱን እንዲያረጋግጥ፣ ከሞላ ደግሞ ከገንዳ ውጪ ሳይጣል ቆሻሻ ለመሰብሰብ የሚዟዟረው መኪና በሚመጣበት ግዜ በጥሩምባ ሲጠራ ወደ መኪናው እንዲያቀርቡ ማስጠንቀቂያ ቀደም ብሎ ስለተነገረ መኪናው ሰፈር ውስጥ ሲገባ የማዘጋጃ ቤት የጽዳት ሠራተኞች ጥሩምባ እየነፉ ‹ቆሻሻ አውጡ› ሲሉ ቆሻሻውን ያወጣሉ፡፡ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ ተብሎ አማካይ ቦታዎች ላይ

ከተቀመጡት ገንዳዎች ውጭ ቆሻሻ የጣለ ግለሰብ ይቀጣል፣ ፍ/ቤት እን ኳን አይኬድም ነበር፣ እዛው ጽዳት ቢሮ ነበር ቅጣቱ የሚከናወነው።"

በዚህ ወቅት የፓርክና የመናፈሻ ክፍል፣ የመንገድ ጥገና ክፍል፣ የጽዳትና ጤና ጥበቃ ክፍል የሚመራው በኢንጂነር ጌታቸው ኃላፊነት ሥር ነበር። ወደ ከፍታና ቶፖግራፊ ክፍል ሲዛወሩ የፓርክና መናፈሻ ክፍሉ ከኢንጂነር ጌታቸው እጅ አልወጣም።

ኢንጂነሩ ቀጣዩ ሥራቸው በካርታና ቶፖግራፊ ውስጥ በምክትል ኃላፊነት ደረጃ ነበር። ይህ ክፍል ይመራ የነበረው ፕሮፌሰር ጉላቲ በሚባል የሕንድ ተወላጅ ነበር። በዚህ ክፍል ውስጥ ብዙ ጠቃሚ ልምድ እንዳገኙበትም ኢንጂነሩ ይናገራሉ። በዚህ ክፍል የአዲስ አበባን ትክክለኛ ገጽታ ለማወቅ በተለያየ ጊዜ ከአየር የተነሱትን ካርታዎች ደጋግመው የማገላበጥና የመመልከት ዕድል አግኝተዋል።

በካርታና ቶፖግራፊ ክፍል ውስጥ ስላገኙት ተሞክሮም ሲገልፁ "ለማንኛውም የከተማ ልማት ጥናት መሠረታዊ መነሻ የሚሆኑት የመንገድ አውታሮች፣ ገደልና ሜዳውን፣ ወንዙንና ሸንተረሩን፣ ሕንፃ የሰፈረበትንና ባዶውን ቦታ ሌሎችንም ለከተማ ዝርዝር ጥናት የሚጠቅሙ መረጃዎችን እንድገነዘብ፣ የተማርኩትንም እንድከልስ አስችሎኛል።" ብለዋል።

ኢንጂነር ጌታቸው በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትዕዛዝ ሰኔ 12 ቀን 1955 ዓ.ም ወደ ፕላን ክፍል እንዲዛወሩ ተደረገ። በዛን ወቅት የቤት ሥራ ፈቃድ ክፍልም በፕላን ክፍል ሥር ነበር።

ወቅቱ የውጭ ሃገር ኤክስፐርቶች ከድርጅቱ ለቀው የመሥሪያ ቤቱ ቴክኒካዊ ክፍሎች በኢትዮጵያውያኖች ባለሙያዎች የሚካሄድበት ጊዜ ጎልቶ የታየበት ወቅት ነበር።





ኢንጂነር ጌታቸው የፕላን ክፍል ኃላፊ ሆነው ሥራውን እንደተረከቡ ሥራውን ለማቀላጠፍና ውጤታማ ለማድረግ የተወሰኑ ማሻሻያዎች አድርገዋል። ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

1. ሥራዎቹን በሥራ ጣቢያቸው መልክ መልክ አስያዙት፣
2. ለየሥራውም በተለያዩ ቦታዎች ብቃት አላቸው ብለው የሚያምኑባቸውን ሙያተኞችንና ሌሎችንም ሠራተኞች መደቡ፣
3. ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ሥራውንና ኃላፊነቱን የሚያስረዳ መመሪያ ቀርፀው አደሉ፣
4. ከውዝፍ ሥራ የዕለት ተዕለት ሥራ ቅድሚያ እንዲሰጠው አደረጉ፣
5. ተከማችቶ ለነበረው ሥራ የሠራተኛ ሃይል መደቡ፣

በመሠረቱ አንድ ሚሊዮን ተኩል ሕዝብ በሚኖርበት ከተማ በየቀኑ የሚቀርቡትን አያሌ ጥያቄዎች በአንድ ቢሮ ማስተናገዱ በጣም አስቸጋሪ እንደነበር ኢንጂነር ያስረዳሉ። ከተማ ላይ ቤት የሚሠሩ፣ ካርታ የሚያወጡ፣ መሬት የሚገዙ የሚሸጡ ግለሰቦች የፕላን ክፍልን ማረጋገጫ ስለሚፈልጉ ዝርዝር ጥናት ባልወጣለት ከተማ የመንገዱን አቅጣጫ ስፋት፣ ምን ዓይነት ሕንፃ እንደሚሰሩ፣ በአጠቃላይ አዲስ ፕሮጀክት የማይነካው ለመሆኑ ዘለቄታ ያለው ማረጋገጫ መስጠቱ አዳጋች ነበር።

ለዚሁም ነበር ኢንጂነር ጌታቸው ለማስተር ፕላኑ ከፍተኛ ትኩረት የሰጡት። የመጀመሪያው ማስተር ፕላን በ1950ዎቹ ውስጥ ከአዲስ አበባ ሕዝብ ብዛት መጨመርና ከተለያዩ ክፍላተ ሃገራት ሰዎች ወደ አዲስ አበባ በመጉረፋቸው ምክንያት የመጀመሪያው ማስተር ፕላን መከለስ አለበት የሚል አቋም ያዙ።

# ምዕራፍ ሰባት

## የማስተር ፕላን ክለሳ

በመሠረቱ ለፓርላማ ቀርቦ ለመጀመሪያ ጊዜ የፀደቀው የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን የተዘጋጀው በእንግሊዛዊው ታዋቂ መሐንዲስ ሰር ፓትሪክ አበር ክሮምቢ ሲሆን፤ መሃንዲሶችን ወደ ኢትዮጵያ ይዘዋቸው የመጡት ከግርማዊ ቀዳማዊ ሃይለሥላሴ ጉብኝት ጊዜ በኋላ በንግሥቲቱ ተመርጠው ነው የተላኩት።

ስለአዲስ አበባ ከተማ የመሪ ፕላን (ማስተር ፕላን) ኢንጂነር ጌታቸው ሲገልፁ፡- "የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ለመጀመሪያ ጊዜ በሰር ፓትሪክ አበር ክሮምቢ ተጠንቶ በአዋጅ የወጣ ማስተር ፕላን ነው።" ማስተር ፕላኑ በ1947 ነበር የፀደቀው።

የመጀመሪያውን ማስተር ፕላን የማዘጋጀቱ ሂደት ብዙ ችግሮች ገጥመውታል። ከነዚህም ችግሮች ውስጥ ዋነኛው በኢኮኖሚና በሶሻል ደረጃ የተሟላ ስታትስቲክስ አለመኖር ነው።

የመረጃዎቹ አለመሟላት ስራውን እንዲጎተት አድርጎታል። ፕላነሩ የብዙ ኢትዮጵያውያኖችን እርዳታ ጠይቀዋል። ወደ ሃገራቸው ተመልሰው ከመሄዳቸው በፊት የጎደሉትን እያጠኑ የሚያሟሉ እንግሊዛዊ ባለሞያዎችን ትተው ሁኔታው በመጠኑ ሲስተካከል ተመልሰው ሥራውን አጠናቀቁ። ሥራውን ለማጠናቀቅ ሦስት ዓመት ፈጅቷል። ከዚህ ሁሉ ድካም በኋላ ነበር ለፓርላማው የቀረበውና የፀደቀው። ከዛም በቁንጽል ማስተር ፕላኑ በተለያዩ የውጭ ኤክስፐርቶች መጠነኛ ክለሳ ተደርጓል።





ኢንጂነር ጌታቸው ማህተመ ሥላሴ ግን መሪ ፕላኑን ሲከልሱ ለ10 ዓመታት እንዲያገለግል የነበረ ሲሆን የመረጧቸው ሶስት ንኡሳን ቦታዎችም የየራሳቸው ምክንያት ነበራቸው። ለምሳሌ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በሃገራችን ሲመሠረት ከተማዋ የዓለም አቀፍ የከተሞች ይዘት እንዲኖራት በማስፈለጉ ነው። ይህ መሪ ፕላን በሃገሪቱ ባለሙያ በሆኑት በኢንጂነር ጌታቸው ሲከለስ የከተማዋ ነዋሪ ቁጥር አንድ ሚሊዮን ተኩል ያህል ደርሶ ነበር። እቅዱ የሚተነትነው ከባድ የጭነት መኪናዎች ወደ ጅማ እና ደሴ ወደሌሎችም ክፍለሃገሮች የሚያልፉት ከባቡር ጣቢያው ግንኙነት ባለው መንገድ እንዲሆን ያስገድዳል። ይህም ለኢኮኖሚው አውታር በዋነኛነት እንቅስቃሴውን ያፋጥናል ተብሎ ስለታመነ ነበር።

ነገር ግን በ1956 ዓ.ም በተከለሰው ማስተር ፕላን ቸርችል ጎዳና ላይ የሚፈጥረውን የትራፊክ መጨናነቅ ለማስቀረት ተሞክሯል። ይህም የሆነው አዳዲስ መንገዶችን በመቀየስ ሲሆን ከሜክሲኮ አደባባይ ተነስቶ በሰሜን አቅጣጫ ወደ ተክለሃይማኖት አካባቢ የሚያመራ መንገድ ነው። በተጨማሪም በኮልፌ በኩል በአቃቂ ወንዝ ወደ ደብረዘይት በደቡብ ምሥራቅ እስከ አባዲና የሚዘልቅ አዲስ መንገድ በማስተር ፕላን ተቀይሶ እንደነበር በወቅቱ የነበረው ጥናት ያመለክታል።

ኢንጂነር ጌታቸው ስለ ማስተር ፕላኑ ሲናገሩ "የተዘጋጀው ማስተር ፕላን ነው እንጂ ወደ ዝርዝር ጥናቱ አልተገባም። ማስተር ፕላን ስንል በመሠረቱ አስተዳደሩን እንጂ ቴክኒካሉን አይደለም። ይሄ ቦታ ለዚህ፣ ያ ቦታ ለእንዲህ ዓይነት አገልግሎት ተብሎ የመደልደልና እንዲሁም የህዝቡን አሰፋፈር የሚመለከት ወዘተ ነው። ባጭሩ ወደ አስተዳደራዊ ጉዳይ ያመራል። ዝርዝር ጥናት ውስጥ ሲገባ ግን

ቦታን በሴንቲሜትር እስከ መለካት ይደርሳል" ብለዋል።

ዝርዝር ጥናቱን ለመሥራት "ቦልተ እና ሄንስ" የሚባል የእንግሊዝ ኩባንያ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ነበር። ኢንጂነሩ ስለ ኩባንያው ሲናገሩ "ኩባንያው የተወሰነ ነገር ሠርቷል። የከተማውን ዴቨሎፕመንት ፕላን በዚህና በዚያ ቢሠራ ይሻላል በሚል የቤቶችንም አቀማመጥና ዓይነታቸውን እያሳመረ ለመሥራት ሞክሮ ነበር። እነሱም ብዙ አልቆዩም ሄዱ።"

ኢንጂነሩ ወደ ፕላን ክፍል ውስጥ ሲገቡ ብዙ ነገሮችን መመልከትና መመርመር ጀመሩ። አዲስ አበባ በህዝብ ብዛትና ፍልሰት፣ በቤቶች አቀማመጥ፣ በአጠቃላይ በምን ደረጃ ላይ እንደምትገኝ ጥናት አደረጉ። መሠረቱን ሳይለቅ ለልማትና ለዕድገት አጋዥ የሆኑ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን ከለዩ በኋላ መስተካከልና መጨመር ያለባቸውን በመልክ በመልኩ አስቀመጡ።

ኢንጂነር ጌታቸው ማስተር ፕላኑ ሥራ ላይ ያልዋለበትን ሦስት ምክንያቶች ይጠቅሳሉ። "አንደኛ ገንዘብ ማጣት፣ ሁለተኛ ያንን ማስተር ፕላን ለህዝብ አስረድቶና ለሠራተኛውም አስገንዝቦ በማስተር ፕላኑ መሠረት በማስፈጸም ሂደት የሚፈጠር ችግር፣ ሦስተኛ ያ ተጠቃሚው ህዝብ የማስተር ፕላንን ጥቅም እስካልተረዳ ድረስ፣ መሬቱ ዋጋ እንደሚያወጣ እስካላወቀ ድረስ፣ ትብብር እስካላደረገ ድረስ ማስተር ፕላኑ ችግር ይገጥመዋል" ብለዋል።

"ክለሳ" ስለሚባለው ጽንሰ ሃሳብም ማስረጃ እያጣቀሱ ሲያስረዱ የሚከተለውን ብለዋል። "ማስተር ፕላኑ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ለሚደርስ ህዝብ ነው የተሠራው (ለተወሰነ ህዝብ) በደርግ ጊዜ የሰው ቁጥር ስለጨመረ ያ ማስተር ፕላን የግድ መከለስ





ነበረበት። ምክንያቱም የጨመረውን ህዝብ ጥቅም ወይም አኗኗር በሚያመቻች ሁኔታ ማዘጋጀት ይኖራል። ግን ማስተር ፕላኑን በሙሉ አፍርሶ አይደለም። በዚያ ውስጥ የማሻሻያ ነገር ይደረጋል። ዋናው ማስተር ፕላን አይነካም። ለዚህ ነው ክለሳ የሚባለው" ብለዋል።

እሳቸውን በተመለከተ ዋናውን ማስተር ፕላን እንዲከልሱ ያስገደዳ ቸውን ምክንያት ሲገልጹ "አንደኛ የመጀመሪያው ጥናት ለዘጠኝ መቶ ሺህ ሰዎች መኖሪያ ነበር የታሰበው። አሁን ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ እየሆነ ነው። ከማስተር ፕላኑ ውጭ ብዙ ቤቶችም ተፈጠሩ። ከተማ ውስጥ ያሉትን ቤቶች ለማሻሻል ሲፈለግ ባለርስቶቹ ገና ለገና መሬታቸው ከዛሬ ነገ የተሻለ ዋጋ ያወጣል በሚል ለመተባበር ፈቃደኞች አልሆኑም። ልማቱ በሚጠይቀው መሠረት ፈጣን መሻሻል ማድረግ አልቻሉም።" ብለዋል።

በዚህን ጊዜ ኢንጂነር ጌታቸው እስቲ ይፋ የሆነ ማስታወቂያ ላውጣና ባለርስቶቹ ይተባበሩኝ እንደሆን ልሞክር በማለት ማስታ ወቂያ አወጡ። የማስታወቂያው ፍሬ ሃሳብ እንዲህ ይላል፡- "መሃል ከተማ ፒያሳ ያላችሁ በቦታችሁ ላይ በፕላኑ መሠረት ሥሩበት። ወይ ደግሞ ቦታውን ለሚሠራ ሰው ሽጡት። ደህና ዋጋ ታገኙበ ታላችሁ። ሽጣችሁ ባገኛችሁት ገንዘብ ሌላ ቦታ ሄዳችሁ እጥፍ የሆነ ንብረት ታገኛላችሁ......"

በመሠረቱ በጊዜው የግል ንብረትን ከባለቤቱ ፈቃድ ውጭ መንካት በህግ የተከለከለ ስለነበረ፣ ስዎቹም የተጠየቁትን ለማድረግ ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው ኢንጅነሩ ዋናውን የከተማ እምብርት ወደ ብሔራዊ ቴአትርና ወደ ፖስታ ቤት እንዲወርድ አደረጉት። ስለዚህም ሲናገሩ፡- "ከተማውን ወደ ታች ማውረዴ አንድ በግሌ

ያበረከትኩት ነጥብ ነው” ብለዋል፡፡

ከተማው ወደ ብሔራዊ ቴአትርና ወደ ፖስታ ቤት አካባቢ እንዲስፋፋ ጥረት ባደረጉበት ወቅት ቤት ሰሪዎች ቤታቸውን ሲሠሩ በፕላኑ መሠረት እንዲሰሩ ውል እንዲገቡ ተደረገ፡፡

በከተማው መሀል የሚገኙ ወንዞች የሚያስከትሉትን መጥፎ ጠረን ለማስቀረት ወደፊት የሚገነቡ ህንፃዎች ወንዞችን እየሸፈኑ ማለፍ እንዳለባቸው ቀደም ሲል ኢንጂነር ጌታቸው ባጠኑት የአሥር ዓመት ማስተር ፕላን ላይ ተቀምጧል፡፡

በፕላኑም መሠረት የጠቅላይ ፖስታ ቤት ህንፃ የተገነባው “ባንቲ ይቀጡና ቁርጢሚ” እየተባሉ በሚጠሩት ወንዞች ላይ ሲሆን፣ ግዮን ሆቴል መግቢያ በር ላይ የሚገኘው ሼህ አላሙዲ ያሠሩት የናኒ ህንፃ የተገነባው በነዚሁ ወንዞች ላይ ነው፡፡

“በመሠረቱ ማስተር ፕላን መሪ ፕላን እንጂ ተግባራዊ ፕላን አይደለም፡፡ ጊዜንና ባለሙያዎችን የሚጠይቀው ዝርዝር ጥናቱ ነው፡፡ ይህ ዝርዝር ጥናት ኢኮኖሚውን ከማስተር ፕላኑ ጋር ያጣጣመ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ አለበለዚያ ቁንጽል ይሆናል፡፡ ማስተር ፕላን ወጣ ተብሎ ለምን አሁኑኑ ውጤት አላየሁም የሚል አካሄድ ስህተት ነው” ይላሉ ኢንጂነር ጌታቸው፡፡





# ምዕራፍ ስምንት

## ትሮሊባስ፣ ትራምካርና ኮንዶሚኒየም

ኢንጂነር ጌታቸው በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የፕላን ክፍል ሃላፊ ሆነው ሲሠሩ በቼኮዝላቫኪያ ውስጥ በአንድ ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው ትራንስፖርትን የሚመለከት ሰሚናር ላይ እንዲገኙ ግብዣ ቀርቦላቸው ወደ እዛው ሄደው ነበር፡፡

በሴሚናሩ ላይ ቀርበው የነበሩ ሃሳቦችን ማሰላሰል የጀመሩት ገና የጥናት ጽሁፍ አቅራቢዎቹ ሁለት ሦስት ጽሁፎችን እንዳቀረቡ ነበር፡፡ ዋነኛው ማጠንጠኛ ሃሳባቸው ከሃገራችን ጋር የሚስማማው የትኛው የትራንስፖርት ሲስተም ነው የሚል ነበር፡፡ እዛም ላይ ሃገራችን በጊዜው ባለሙያዎች ስለሌሏት እነዚህ ሰዎች በምን መልኩ ሊያግዙን ይችላሉ ብለው አሰቡ፡፡ በኢትዮጵያ በኩል ማቴሪያሉም፣ ገንዘቡም እንደሌለ አወጡ አወረዱ፡፡

በስብሰባው ላይ ታትራ የሚባል የቼኮዝላቫኪያ የትራንስፖርት ኩባንያ ቀልባቸውን ሳበው፡፡ ወደ እነሱ ጠጋ ብለው ወደ አዲስ አበባ ብቅ እንዲሉ የኩባንያውን ሰዎች ጠየቁ፡፡ ሲጠይቁ አዲስ አበባ ሰፋ ያለ ገበያ እንደሚያገኙ አድረገው ጉጉት በመፍጠር ነበር፡፡ ቢመጡ ከኢትዮጵያ ይልቅ እነሱ ይበልጥ ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉም ኩባንያውን ወክለው ለተገኙት ኃላፊ አሳወቁ፡፡

ሰዎቹ ጥቂት ካሰቡበት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት እንዳደረባቸው ለኢንጂነር ጌታቸው ገለጹቸው፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው ስለድርጅቱ፣ ስላለው አቋም ዘርዘር ያለ መረጃ ለማግኘት በሚል "እኔ በመንግስት ውስጥ ያለኝ ደረጃ ዝቅ ያለ ስለሆነ፤ ምን ምን ልትሠሩልን እንደምትችሉ እዚሁ አሁን ብትነግሩኝ ለአለቆቼ ላስረዳቸው እችላለሁ፡፡" አሉ፡፡

አንዳንድ ነገር ያስረዷቸውና "ለማንኛውም በራሳችን ወጪ መጥተን ጥናቱን እናካሂዳለን" አሏቸው፡፡ ኢንጂነር ይሄኔ ትልቅ ተስፋ ጨበጡ፡፡

ከዛም ፋብሪካው ስለሚያመርተው ትራም ካርና ትሮሌባስ ዝርዝር መረጃ ሰጧቸው፡፡ ኢንጂነሩ ነገሩ ጥሩ ነው ግን በኛ በኩል አንዳንድ ችግሮች ስላሉ እዛ ላይ እንድትተባበሩን ያስፈልጋል በማለት ቃል አስገቧቸው እነዚህም ክሬዲት ለመስጠት ፈቃደኛ ስለመሆናቸው፣ ጥናቱን በራሳቸው ገንዘብ ስለማጥናታቸው፣ ባለሙያ እንደሚያስለጥኑላቸው.....ወዘተ

ኢንጂነር ጌታቸው ወደ ሃገር ቤት እንደተመለሱ ካመጧቸው የአውቶቡሶች ስዕል ጋር ሪፖርታቸውን በቀጥታ ለጃንሆይ ሊኖር ከሚችለው ዕድል ጭምር አስረዱ፡፡ ጃንሆይ በነገሩ ተደስቱና "ይህንንማ ብታደርግ ሃገራችንን የፈረንጅ ሃገር አደረካት ማለት ነው" አሉ፡፡

ሥራውን መገናኛ ሚንስቴር እንዲከታተለው፣ጥናቱንም ከኩባንያው ባለሙያዎች ጋር እንዲያጠኑ ተደረገ ኩባንያውም ቃል በገባው መሠረት በራሱ ወጭ ዝርዝር ጥናቱ በሚገባ ተጠናቀቀ፡፡ ቴክኒካል ድሮዊንጉ አልቀረም፡፡ የገንዘብ ወጪው ሲታይ፣ በዛን ጊዜ ገንዘቡ





ከፍ ያለ ዋጋ ያለው ቢሆንም፣ ወደ ሰባት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር ብቻ ሆነ፡፡ ብሩን እነሱ በብድር ሊሰጡ፡፡ ከሁለት ዓመት በኂላ የእዳው ክፍያ እንዲጀመር ስምምነት ተደረሰ፡፡

በመጨረሻም ጥናቱ ተቀባይነት ካገኘና ከተወሰነ በኂላ በ1961 ዓ.ም ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ ነበር፡፡ በወቅቱ ለዚህ ሥራ የተጠየቀው ገንዘብ 30 ትሮሊባሶችን (በጎማ ሆኖ በኤሌክትሪክ ሃይል የሚንቀሳቀስ) 10 ትራምካሮችን (በሃዲድ ላይ ሆኖ በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሽከረከር) ለመግዛትና ለጣቢያዎችም ግንባታ የሚውለውን ወጪ ሁሉ የሚሸፍን ነበር፡፡ ይህንን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች በተጀመረበት ወቅት አብዮቱ ፈነዳ፡፡

የዚህ ጥናት ሙሉ ሰነድ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በእጃቸው እንደነበረ ኢንጂነር ጌታቸው ይናገራሉ፡፡ ይሁንና በቅርብ በአንድ የትራፊክ ኮርስ አውደ ጥናት ላይ ጥናቱን ለማሳየት ወደ ማዘጋጃ ቤት ይዘውት እንደሄዱና ስለ ጥናቱ ለተሳታፊዎቹ ገለፃ እንዳደረጉና "ማየት ማመን ነው" በሚል ሰዎቹ ጥናቱን በዓይናቸው እንዲመለከቱ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጠውላቸው ለሻይ ወጥተው ሲመለሱ የጥናቱን ሰነድ እቦታው ላይ አለማግኘታቸውን ኢንጂነር ጌታቸው ሃዘን በተሞላበት መንፈስ ገልፀዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዋናው ኮፒ አሁንም በመገናኛ ሚኒስቴር አለ፡፡

የኮንዶሚኒየም ሕንፃ መሠረተ ሃሳቡ የተጠነሰሰውም በአፄ ሃይለሥላሴ ሥርዓት ነው፡፡ ስለኮንዶሚኒየም የቁጠባ ቤቶች በሚል ኢንጂነር ጌታቸው የሚሉት አላቸው፡- "በወቅቱ እኔ የአዲስ አበባ

ማዘጋጃ ቤት የፕላን ክፍል ኃላፊ ነበርኩ። የመንግስትና ደህና ደሞዝ የሚከፈላቸው የቀን ሠራተኞች ጭምር የቤት ባለቤት ሊሆኑ የሚችሉበት መንገድ ከንዶሚኒየም መሆኑን የሚገልጽ ጥናት ለአፄ ሃይለሥላሴ አቀረብኩ። ጥናቱም ተቀባይነት አገኘ። ይህንንም ጥናት ላቀርብ የቻልኩት ከጣሊያንና ከእንግሊዝ ከጀርመን ልምድን በመቅሰም ነበር። ለመገንባት የታሰበው ‹ቮልካኒክ አሽ› ፓሚሽ እየተባለ በሚጠራ ከአዋሽ እስከ አዋሳና እስከ ደብረዘይት መንገድ ድረስ ባሉት አካባቢዎች በብዛት ከሚገኝ የሳተገሞራ አመድ ነው። ይህም ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት አምስት ኩንታል ፓሚሺ ወደ ቡልጋሪያ ተወስዶ አስፈላጊው የላብራቶሪ ምርመራ ተደርጎለታል። በውጤቱም ፓሚሽ ውሃና ድምጽ የማያሳልፉ (ወተር ኤንድ ሳውንድ ፐሩፍ) መሆኑን፣ ክብደትም የሌለውና ለግንባታ በጣም ጥሩ መሆኑ ተረጋግጧል። ከዛም ባለፈ በሳንቃ መልክ እየተመረተ ለገበሬዎች ቤት መስሪያ እንደሚጠቅም ጥናቱ ያጠቃለለ ነበር። ፋብሪካው ከሚያመርትበት እስከ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ድረስ ተወስዶ ቢሠራበት አትራፊ ፕሮጀክት መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጦ ነበር ስርነቀሉ ለውጥ ጥሩውንም ሃሳብ ነው ነቅሎ የጣለው።





# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ብሔራዊ ሃብት ልማት ኮርፖሬሽን ሼር ካምፓኒ (ብሀል)

“ብሔራዊ ሃብት ልማት ኮርፖሬሽን ሼር ካምፓኒ (ብሀል)” የሚል ሥም የተሰጠው ኩባንያ ህልውና የተፈጠረው በኢንጂነር ጌታቸው ማህተመሥላሴ ልዩ አስተውሎትና እንቅስቃሴ ነው። ምክንያቱም ከሥር መሠረቱ የድርጅቱ መሥራችና ሃሳብ አመንጪ ብቸኛው ሰው እሳቸው ነበሩና።

ሃሳቡ የመጣላቸው ፕላን ክፍል ውስጥ በሃላፊነት በሚሠሩበት ጊዜ ነበር። ሥራዎች፣ ሁሉም ማለት ይቻላል፣ ፈቃድ አግኝተው ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግባት በፕላን ክፍል ውስጥ ማለፍ ነበረባቸው።

ኢንጂነር አንድን ሂደት ደጋግመው ተመለከቱ። አንድ ነገር ዲዛይን ተደርጎ ለፈቃድ ሲመጣ፣ የሚመጣው ሥራ ሁሉ ለፈረንጆች ብቻ የተመደበ ይመስል ሁሉንም ሥራ የውጭ ሃገር ሰዎች ሲወስዷቸው አስተዋሉ።

ሥራዎች ለጨረታ ሲቀርቡ፣ አሁንም የጨረታው አሸናፊ የሚሆኑት ኮንትራክተሮች ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል ፈረንጆቹ ናቸው ጨረታውን ጠቅልለው በእጃቸው የሚያስገቡት። ይሄ ነገር ወዴት እያመራ ነው እያሉ ኢንጂነር ጌታቸው ለብቻቸው ተብከነከኑ።

ፈረንጆቹ ጨረታውን ካሸነፉ በኋላ ደግሞ ለሥራው እንቅስቃሴ

የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች የሚገዙት ከወገኖቻቸው ከፈረንጆቹ ሱቅ ብቻ ሆነ።

የመንገድ ሥራውም፣ ሆነ የህንፃ ሥራ እንዲሁም ታላላቅ መካኒካል የሆኑ ሥራዎች ሁሉም ነገር ተጠቃሎ በፈረንጆች እጅ መግባቱ ኢንጂነሩን እንቅልፍ ነሳቸው። በባለሙያ ደረጃ የላቀ እውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያኖች ቢኖሩም ተወዳድረው ማሸነፍ ባለመቻላቸው ፈረንጆቹን የበላይ ሆነው አገኛዋቸው። በፎርማንነት ሥራውን በብቃት የሚያከናውኑት ኢትዮጵያውያኖች ሆነው ሳለ ሥራው ላይ ትርፍ የሚገኙትም ፈረንጆች ብቻ ሆኑባቸው። በኢትዮጵያ ሃብትና ሥራ ላይ የሚታየውን የፈረንጆች የበላይነት ብሔራዊ ስሜታቸው ሊቀበለው አልቻለም።

“መቼ ነው እኛ እራሳችንን የምንችለው? ራሳችንን ችለንስ መቼ ነው በገንዘብና በልምድ የበላይነት ካላቸው ፈረንጆች ጋር ተወዳድረን በማሸነፍ ሥራውን በበላይነት ወይም በእኩልነት የምንመራው?” የሚሉ ጥያቄዎች አእምሯቸው ውስጥ ማመላለስ ጀመሩ።

መጨረሻ ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠሩ ሥራዎችን ለመሥራት ልምድም ገንዘብም ያለው ኢትዮጵያዊ መኖር አለበት ካሉ በኋላ፣ ባለ ጉልበት ማነው? ብለው ራሳቸውን ሲጠይቁ ያገኙት መልስ አንድና አንድ ብቻ ሆኖ አገኙት። “የኢትዮጵያ መንግሥት ነው ጉልበት ያለው” ብለው ደመደሙ።

በመቀጠልም መንግሥት ምን አለው? ለሚለው ጥያቄ መልሳቸው ቅርብ ነበር። መንግሥት ሰፊ የእርሻ መሬት አለው፣ ቤቶች አሉት፣ በተለይ በመንግሥት ንብረት ሚኒስቴር ሥር የሚተዳደር በርካታ ሃብት እንዳለ ተገነዘቡ። ይህ ሃብት ከባንክ ገንዘብ ለመበደር





የሚያስችል አቅም ስላለው ገንዘብ ተገኘ ማለት ነው። በእርግጥ የመንግሥት ንብረት ሚኒስቴር መ/ቤት ያለውን ከመጠበቅ አልፎ ሄዶ ልማትን በብቃት የሚያካሂድ አልነበረም።

በማስከተል የወሰዱት እርምጃ ችግሩን ከመፍትሄው ጋር ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማቅረብ ነበር። ባጭሩ “ኢትዮጵያውያኖች አሁን ባሉበት ሁኔታ ከቀጠሉ ምን ጊዜም ቢሆን እራሳቸውን አይችሉም። ፈረንጆቹ በገንዘብም በሙያም የበላይ ሆነው የሚቀጥሉበት ሁኔታ ነው አሁን ያለው። ስለዚህ እነዚህን የፈረንጅ ኩባንያዎች ሊቋቋም የሚችል ኢትዮጵያዊ ኩባንያ መቋቋም አለበት” በማለት ሃሳብ አቀረቡ።

ጃንሆይ “ይሄ እንዴት ነው ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው?” ሲሉ ይጠይቃሉ።

“መንግሥት እራሱ በጉዳዩ ሊገባበት ይችላል። ንብረት አለው፣ መሬት አለው፣ ቤቶች አሉት፣ ባለሙያዎችን ለማሰባሰብ አቅም አለው……” በማለት ዘርዝረው ካስረዱ በኋላ አንድ ሁሉን ዓይነት ሥራ የማከናወን ፈቃድ ያለው ኢትዮጵያዊ ኩባንያ እንዲቋቋም ጠየቁ።

“ሥራው ማንን ነው የሚመለከተው?” ሲሉ ጃንሆይ ጠየቁ።

“ገንዘብ ሚንስቴርን ነው።”

ወዲያውኑ ይሁን በማለት ሁኔታውን የሚያብራራ ደብዳቤ በጊዜው የገንዘብ ሚንስቴር ለነበሩት ለክቡር ለአቶ ይልማ ደሬሳ ተፃፈ። ደብዳቤው ኢንጂነሩ ለጃንሆይ ካቀረቡት ማመልከቻ ጋር ተያይዞ ነበር ለአቶ ይልማ ደሬሳ የቀረበላቸው።

መንግሥት የራሱን ሼር ኩባንያ ማቋቋሙ የፈረንጆችን የበላይነት ለማስ ቀረት ብቻ ሳይሆን ጥቅሙ ዘርፈ ብዙ ነው። ወደ ውጭ የሚወ

ጣውን ቁሳቁስና ገንዘብ እንዲቆጣጠር ያስችለዋል፡፡ ታክስ በአግባቡ መከፈሉን ለመቆጣጠርም ያግዛል፣ የውጭ ኢንቬስተሮች ባጭር ጊዜ ትርፍ በሚያስገኙ ኢንቨስትመንቶች ላይ ብቻ እንዳይሰማሩ ለመከላከል ይረዳል፣ በአክሲዮን ሽያጩ ላይ ደግሞ መንግሥት የተሻለ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ የተዛባ ጨረታ እንዳይኖርም ትልቅ መቆጣጠሪያ ዘዴ ነው በሚል ውሳኔ ላይ ተደረሰ፡፡ ኩባንያውን ለመመሥረት የትኞቹ ንብረቶች ቢሆኑ ይሻላል የሚለው መረጣ ተጀመረ፡፡ ኢንጂነር ጌታቸው ለቦታው አስፈላጊ መሆናቸው ጎልቶ በመምጣቱ ኩባንያውን ለማቋቋም ከማዘጋጃ ቤት ወደ መንግስት ንብረት ሚኒስቴር ስራ እንዲዛወሩ ደብዳቤ ደረሳቸው፡፡

ኢንጂነሩ ሥራቸውን እንደጀመሩ ወዲያውኑ በየክፍለ ሃገሩ በመዞር ለኩባንያው ይጠቅማሉ ያሏቸውን የመንግሥት ንብረቶችን መዘገቡ፣ መታደስ የሚገባውን እንዲታደስ አደረጉ፣ ንብረቶቹ የኩባንያው ህጋዊ ንብረት እንዲሆኑ በማድረግ ብሔራዊ ሃብት ልማት ኮርፖሬሽን ሼር ካምፓኒ እንዲመሠረት ተደረገ፡፡

ኩባንያውን የመመሥረት ሃሳብ አመነጩ፣ ኩባንያውም ህጋዊ ህልውና እንዲኖረው፣ እንዲሁም የከፍተኛ ካፒታል ባለቤት እንዲሆንና ሌሎች መሰል ስራዎችን ካከናወኑ በኋላ ኢንጂነር ጌታቸው ፈጽሞ ያልጠበቁት ነገር ተከሰተ፡፡

ለኩባንያው የተሾሙት ሥራ አስኪያጅና ማኔጂንግ ዳይሬክተር ሥሞች በይፋ በማስታወቂያ ወጣ፡፡ እነዚህንም የመንግስት ንብረት ሚኒስቴር ምክትል ሚንስትር የነበሩት አቶ ዘውድነህ ቅጣው ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ሚንስትር ድኤታ የነበሩት ፊታውራሪ ሃይለሚካኤል ደግሞ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ሆነው እንዲሠሩ በቦርዱ ሹመቱ ተሰጣቸው፡፡





ኢንጂነር ጌታቸው ለሰዎቹ የተሰጠው ሹመት ግርምታ ቢፈጥር ባቸውም መገለላቸውን አምንታዊ ከሆነ የተለያየ አቅጣጫ ተመልክ ተውታል፡፡ "ኩባንያው በ25 ሚሊዮን ብር ካፒታል ስለተቋቋመ ለሥራው ረዘም ያለ የስራ ልምድ ያላቸው ሰዎች ተፈልገው ይሆናል፣ በወጣትነቴ ምክንያት ይሆን ይሆናል ኃላፊነቱ ያልተሰጠኝ፣ ዋናዎቹን ባለሥልጣናት ሃሳቡ ሲጠነሰስ ባለማማከሬ በተፈጠረው ዱብ እዳ እነዚህን ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ከሥራ ገበታቸው ማንሳቱ ቅሬታ ስለሚፈጥር ታስቦ ከኩባንያው የማኔጂንግ ዲሬክተርነት በተጨማሪ የመንግስት ንብረት ሚኒስቴር ኃላፊነቱን እንደያዙ እንዲቆዩ መደረጉ ችግሩን ስለሚአመለክት ቅሬታ አላደረባቸውም ነበር፡፡ ሆኖም……" በማለት አሰቡ፡፡

ለሥራውም እንዳልተፈለጉ እርግጠኛ ሲሆኑ በቢሯቸው የነበሩ የግል መጻህፍቶቻቸውን ሰብስበው፣ ቢፈለጉ ሊገኙ የሚችሉበትን የስልክ አድራሻ አስቀምጠው "እኔን አልተጠቀማችሁብኝም፣ ባይሆን ቢሮውን ተጠቀሙበት" የሚል መልእክት ትተው ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡

ኢንጂነሩ በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አሰቡ እናም ወሰኑ፡፡ በጊዜው የነበራቸው ንብረት የወዳጃቸውን ቤት ካርታ አስይዘው ከባንክ አስራ ስምንት ሺ ብር ተበድረው የሠሩት ቤታቸው ብቻ ነበር፡፡ ይህንን ቤት ከነቤት እቃው መሸጥ ነበረባቸው፡፡ ለአምስት ዓመት ያህል የባንክ ዕዳቸውን ሲከፍሉ ቆይተው የቀረባቸውን እዳ በመሸጥ ከፍለው ከዘጉ በኋላ አንድ ክፍል ቤት ተከራይተው ልጃቸውንና ባለቤታቸውን ይዘው ወደ ተከራይዋት አንዲት ክፍል ቤት ገቡ፡፡ ይህን ሲያደርጉ ግን አንድ ውሳኔ ላይ ደርሰው ነበር፤ ወደ እርሻ ሥራ ለመግባት፡፡



የኢንጂነር ጌታቸው የግል እርሻ ቦታ

ወደ ቆላው ወደ መቂ ወረዱና ግብረ ጠል የሆነ አምስት ጋሻ መሬት በጨረታ አሸንፈው በሦስት ሺህ ብር ገዙ፡፡ በዛው ሰዓት የአሜሪካን ኤምባሲ መኪና በጨረታ ይሸጥ ነበርና አንድ ፒክ አፕ መኪና በአንድ ሺህ አንድ ብር በመጫረት በአንዷ ብር ብልጫ ምክንያት የጨረታው አሸናፊ በመሆን መኪናዋን በእጃቸው አስገቡ፡፡ አሚራን ከሚባል የእሥራኤል ኩባንያ መሬታቸውን አሳይተው ቅድሚያ ክፍያ በመክፈል በክሬዲት አንድ ትራክተር ወሰዱ፡፡

ከቤቱ ሽያጭ ወደ አስራ ሦስት ሺህ ብር ተርፏቸው ስለነበር፡፡ በዛው ገንዘብ ሠራተኞች ቀጠሩ፡፡ ሠራተኞቻቸው ወደ ኋላ ላይ ብዛታቸው ወደ ሰላሳ ደርሰው ነበር፡፡ ምንጠራውን አካሄዱ፡፡ ዘርም በክሬዲት ወሰዱ፡፡

እርሻው መልካም ፍሬን አፈራላቸው፡፡ ሜካናይዝድ የሆነ እርሻን አደ





ራጁ፡፡ የጭቃ ቤታቸውን ሠሩ፤ ለእሳቸውም፣ ለሠራተኞ ቻቸውም፡፡

በቆሎው ተመረተ፣ ቦለቄ ተመረተ፣ ጤፍም አልቀረም፣ ፍራፍሬ ውንም ቢሆን ሞካከሩት፡፡ ያ በአምቦ እርሻ ኮሌጅ የተማሩት ትምህርት እዚህ ቦታውን ያገኘ መሰለ፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው ለአዲስ ነገር ፊር ቀዳጅ ካሰኟቸው ምክንያቶች በዋነኛነት በሰፊው የሚጠቀሰው በቆራጥነት ከመንግስት ሥራ ለቀው የግል ሠራተኛ በመሆን ለሌሎችም ምሳሌ በመሆናቸው ነው፡፡

ከኢንቨስትመንት ባንክ ገንዘብ ተበደሩና የውሃ ጉድጓድ አስቆፈሩ፡፡ ለሙከራ የተተከለው የፍራፍሬዎች ምርት ልዩ ሆነ፡፡ ብርቱካኑ፣ ሎሚው እንዲሁም ቃሪያው፣ በርበሬው በደንብ ያዘ፡፡ ምርቱ እሳቸውን ብቻ ሳይሆን ጎረቤትንም አስደነቀ፡፡



የኢንጂነር ጌታቸው የግል እርሻ ቦታ

ኢንጂነሩ የአከባቢውን ገበሬ ለማገገዝ እንቅስቃሴ ጀምረው ነበር፡፡ ከእሳቸው እርሻ ወደ ሦስት ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ ባህር

አለ። ባሕሩ በክረምት ይሞላል። ከዛ ባህር በላስቲክ ፓምፕ ወደ መንደርዋ በማምጣት የአከባቢው ገበሬዎች ከብቶች ውሃ እንዲያገኙ ለአትክልትና ፍራፍሬም እንዲጠቅም ነበር እቅዳቸው፣ በመሠረቱ እዛው ተጠቃለው ለመኖር ነበርና ሃሳባቸው።

በእርሻቸው ላይ የቆዩት አንድ ዓመት ከጥቂት ወራቶች ብቻ ነበር። በእርሻው ላይ ሰፊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደገቡ በመካከሉ እሳቸው ከእርሻ ወደ ከተማ እንዲመለሱ አንድ ወሳኝ ምክንያት ተከሰተ። የመጀመሪያውን ሃሳብ በማመንጨት በእግሩ እንዲቆም የታገሉለት ብሔራዊ ሃብት ልማት ኮርፖሬሽን ሼር ካምፓኒ በኦዲተሮች ሲመረመር ኪሳራ ውስጥ ገብቶ ተገኘ።

የኩባንያው ሃላፊዎች ኩባንያውን ብቻ ሳይሆን የመንግስት ንብረት በሆኑ ሃብቶች ላይ ተቆጣጣሪ ሆነው ስለሚሠሩ የኩባንያውና የመንግስት ንብረቶች ተደበላለቁና ምስቅልቅሉ ወጣ። አንድ ንብረት ለእገሌ ይሰጥ ሲባል፣ የኩባንያውም ንብረት ተነስቶ ተሰጥቷል። ገንዘብም ከአንዱ ወደ አንዱ ተመሰቃቅሏል። ይሄ ሁሉ ትርምስ ኩባንያውን ኦዲት ባደረገው አንድ ማንጁድ የተባለ የእንግሊዝ ኩባንያ ሪፖርት ላይ በዝርዝር ቀርቧል።

በኩባንያውና በቦርዱ ውስጥ ሁኔታው ድንጋጤ ፈጠረ። ይሄ ኩባንያ እንዴት ነው ከጅምሩ የተቋቋመው የሚል ጥያቄ ተነሳ። ይህ ጥያቄ ሊጠየቅ የቻለው በአዲሱ የገንዘብ ሚኒስቴር የቦርድ ሊቀመንበር ሲሆን የኢንጂነር ጌታቸው ሥም ቀዳሚ ሆኖ ተጠቀሰ። እስቲ ይጠሩ ይባልና፣ ተጠሩ። "እባክህን እርዳን" የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው። ክፍያ የለውም። ለነገሩ ኢንጂነር ጌታቸው ያኔ ሥራውን በለቀቁ ጊዜ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሥራ ሳይሰሩ ደሞዛቸው አልተቋረጠም ነበር።





ኢንጅነር ጌታቸው ኩባንያውን ከጥንስሱ ያውቁት ነበርና ነገሮችን ለማስተካከል ጊዜ አልፈጀባቸውም። "ይሄ ንብረት አለአግባብ ወደ ሌላ ሄዷል፣ ይሄ ገንዘብ በውዝፍ ሰው እጅ ላይ ያለ ገንዘብ ነው፣ ይሄ ኪሳራ ነው፣ ይሄ ደግሞ ሊሠራ ሲገባ፣ ሳይሠራ ቆይቶ ነው…." በማለት የተሟላ ሪፖርት አቀረቡ።

ሪፖርታቸውን ባቀረቡ በሦስተኛው ቀን ቦርዱ ጠራቸው። ወደ ተጠሩበት ቦርድ ሲቀርቡ "እባክህን የጄነራል ማናጀርነቱን ሃላፊነት ወስደህ ኩባንያውን አስተዳድርልን" የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው።

መልሳቸውን ለማስታወቅ አንድ ሁለት ቀን ይሰጠኝ ብለው ጥያቄ አቀረቡ። ቦርዱ በጥያቄአቸው ተስማማ። እሳቸውም ለአባታቸው ለብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ሁኔታውን ነግረው ምክር ጠየቁ። አባት "አንተ ከኩባንያው እንድትገለል ያደረጉት ሁለቱ ሰዎች በቦታው አሉ ወይ?" ብለው ጠየቁ። "እነሱ ተነስተው ነው" የሚል መልስ ሰጡ ኢንጅነር ጌታቸው። "እንግዲያውስ ጥሩ ነው። ግባና ሥራ" አሏቸው።

ኢንጂነር ሥራውን በዋና ሥራ አስኪያጅነት መምራት ጀመሩ። ይህን ሥራ ሲጀምሩ የበጀት ዓመቱ የቀረው ጊዜ ሦስት ወር ብቻ ነበር። የሚሰራውን ሥራ አሰሩ፣ መሰብሰብ ያለበትን ገንዘብ እንዲሰበሰብ አደረጉ። በዓመቱ መጨረሻ ሂሳቡ ኦዲት ሲደረግ፣ ኩባንያው ከኪሳራ ወጥቶ ሦስት መቶ ሺህ የተጣራ ትርፍ ማግኘቱ ተገለጸ።

እዚሁ ሥራቸው ላይ እያሉ የእሁድ ገበሬ እንደሚባለው አልፎ አልፎ ጊዜ ሲኖራቸው እርሻቸውን እየሄዱ ይመለከቱ ነበር። አንድ ያልተማረ ግን ታታሪ የእርሻ ልምድ ያለው ሠራተኛቸውን በእርሻቸው ላይ በዋናነት መድበው እሳቸው ሙሉ ትኩረታቸውን

ወደ ኩባንያው አደረጉ።

ኮርፖሬሽኑ ጥሩ መንቀሳቀስ ጀመረ። መሻሻል የሚገባውን እንዲሻሻል አደረጉ። የሚታደሰውም ታደሰ። በኢንቨስትመንት፣ በፋይናንስ፣ በቴክኒክና በግብርና ያሉትን የሃላፊነት በታዎች የተማሩ ሰዎች እንዲይዙት አደረጉ። እነዚህ የተማሩ ሰዎችን ለቦታው ብቁ መሆናቸውን የፈተንዋቸው የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ባለሙያዎች ሲሆኑ፣ ኢንጂነሩ ፈተናው ሲሰጥ በታዛቢነት በመመልከት ብቻ ነበር የተወሰኑት።

የተማሩ ሰዎች ቦታ ቦታቸውን ከያዙ በኂላ ኩባንያው በሚሠራቸው ሥራዎች ላይ ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ካፒታል ለማግኘት ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ጠለቅ ያለ ድርድር ማድረግ ተጀመረ። 51% ለኩባንያችን ሲሆን 49% ለውጭ ኢንቨስተር እየሆነ ኩባንያ ተቋቋመ።

ኩባንያው ሲያካሂዳቸው ከነበሩ ሥራዎች ዋና ዋናዎቹ፡-

1. የአባድር የጥጥ እርሻ ከእስራኤሎች ጋር፣
2. የመልካ ሰዲ የሙዝ እርሻ ከኢጣሊያኖች ጋር፣
3. የሥጋ ንጥር ከጃፓኖች ጋር
4. በበቃ የተቋቋመው የቡና ተክል ሥራ ከፈረንሳዮችና ከጣሊያኖች ጋር፣
5. የጉለሌ የብርጭቆና ጠርሙስ ፋብሪካ ከኢንቨስትመንት ባንክና ከግለሰቦች ጋር፣
6. ሠንቀሌ ላይ በ3,000,000.00 (በሶስት ሚሊዮን ብር) የተቋቋመው አዲስ የአምቦ ውሃ ፋብሪካ በኩባንያው ካፒታል ብቻ የተሠራ፣





7. የውሽውሽ የሻይ ተክል ጥናት ኩባንያው በቀጠራቸው የውጭ ኤክስፐርቶች ተጠንቶ ከአፍሪካ ዴቬሎፕመንት ባንክና ከእርሻ ባንክ ብድር ለማግኘት የተስማሙበት ጥናት፣
8. ሆቴሎችና መዝናኛ ስፍራዎችን በተመለከተ (ኢትዮጵያ ሆቴል፣ አዲስ አበባ ከተማ ፍልውሃ ሆቴሎችና መዝናኛዎች፣ ሶደሬ፣ አምቦና አዋሳ ፍልውሃና መዝናኛዎች፣ ይርጋለም ጊዳቦ በሚባለው ፍልውሃ ላይ ያለውን መታጠቢያና ሌሎችንም) ማሻሻል፣
9. ሕንፃና ሌሎችንም የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ያጠቃለለ Real State Development ሼር ኩባንያ ከእርሻ ባንክ ጋር፣
10. ከሳባ የጠጅ ፋብሪካ ጋር የተቋቋመው የአባድር የወይን ጠጅ ምርት፣
11. ከሐዋሳ የእርሻ ጣቢያ ጋር የቃጫ ተክል ልማት፣
12. ሊሙ ውስጥ ያሉ የቡና ልማት እርሻዎች፣
13. አባድር ላይ ስፊ የፍራፍሬ እርሻ፣
14. የውድቅዳቂ ብረቶች ማቅለጫ ፋብሪካ (ከጣሊያኖች ጋር)
15. ጊዳቦ ላይ የለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ ለማቋቋም ጥናቱ ያለቀና ማሽኒያው የተዘጋጀ፣
16. ትሬዠሪ ቢል ከመንግስት ተጫርቶ መግዛት፣
17. ከቡልጋሪያኖች ጋር መተማ ላይ የከብት እርባታንና እርሻ ለማቋቋም ስምምነት ተደርጎ እነሱ ቦታውን ከጎበኙ በኂላ መንገዱንም እራሳቸው ለመሥራት ድርድር የተደ ረገበት።

ሥራዎቹ ውጤታማ እየሆኑ ቢሄዱም፣ አንዳንድ የውጭ ሃገር ኩባንያ ተቀጣሪዎች አለአግባብ የሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ወደ ወንጀል ውስጥ ገብተው ተገኙ። አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት

ከተንቀሳቀሱ የውጭ ሃገር ዜጎች መካከል አንድ እሥራኤላዊና አንድ ህንድ ይገኙበታል። ኢንጂነር ጌታቸው ነገሩን ተከታትለው እሥራኤላዊውን እስከማሳሰር ደርሰው ነበር።

ነገሩ እንዲህ ነው፤ አንድ የህንድ ዜግነት ያለው የሂሳብ ሹምና አንድ እሥራኤላዊ ማናጀር ይመሳጠሩና ለደሞዝ ክፍያና ለሥራ ማስኬጃ በሚል ከባንክ በርከት ያለ ገንዘብ ያወጣሉ። ገንዘቡን ይወስዱና ቤታቸው ያስቀምጡታል። ከዛ የሂሳብ ክፍሉን በእሳት ይለኩሱታል። የሂሳብ ክፍሉ በእሳት ሲያያዝ፣ ከባንክ ያወጡትም ገንዘብ አብሮ ተቃጠለ ብለው ሪፖርት ለማድረግ አስበው ነበር። ባጋጣሚ ቃጠሎው ብዙም ሳይከፋ ከፊሉ ጠፋ።

ኢንጂነር ጌታቸው ይቺን ሪፖርት ለማመን ተቸገሩ። እሳቱ ከምን ሊነሳ ቻለ የሚለውን ማጣራት አደረጉ። በዚህ የማጣራት ሂደት በጊዜው የመብራት ሃይል ባለሥልጣን ከፍተኛ ኃላፊ የነበሩትን የወንድማቸውን የክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴን እርዳታ ጠየቁ። እሳቱ በኤሌክትሪክ ምክንያት ተነስቶ እንደሆነ ሲጣራ ሀሰት ሆኖ ተገኘ።

ሌሎቹንም አስፈላጊ ማጣራቶች ካደረጉ በኋላ፣ ወዲያውኑ የሰዎቹ ቤቶች እንዲፈተሽ አደረጉ። ገንዘቡ ማናጀሩ ቤት ውስጥ ተገኘ። አሳሰሩት።

የእስራኤል አምባሳደር ዜጋዬ ታሠረ በማለት በጊዜው የገንዘብ ሚንስቴር ሚንስትር ለነበሩት ለአቶ ማሞ ታደሰ ኢንጂነር ጌታቸውን ወንጅሎ አመለከተ። አቶ ማሞ የኩባንያው ቦርድ ሊቀመንበር ስለነበሩ ኢንጂነር ጌታቸውን አስጠርተው ስለ ሁኔታው ጠየቋቸው። ኢንጂነር ጉዳዩን ዘርዘር አድርገው አስረዱ። አቶ ማሞ ለእስራኤል አምባሳደር





ይደውሉና "በጉዳዩ ላይ ከኢንጅነር ጌታቸው ጋር ተነጋገር" ይሉና ስልካቸውን ይዘጋሉ።

አምባሳደሩ ወደ ኢንጂነር ጌታቸው መጡ። ተነጋገሩ። ሁኔታው አላዋጣ ሲላቸው "እኔ ሃላፊነቱን እወስዳለሁ ይፈታልኝ። በዛ ላይ እታሠረበት ቦታ ታሟል" በማለት ተማጽኗቸውን አቀረቡ።

አምባሳደሩ ሃላፊነት እንደሚወስዱ ከፈረሙ በኋላ ሰውዬው ተፈታና ከሃገር እንዲወጣ ተደረገ። የእሱ ከቦታው ላይ መነሳት ለኢንጂነር ጌታቸው ኢትዮጵያውያኖችን በቦታው ላይ ለመተካት ዕድል ሰጣቸው። ዕድሉንም ተጠቅመውበታል።

ሌላም ታሪክ አለ፡- እሥራኤላውያኖች ትራክተሮች ከውጭ ያስመጣሉ። ሲያስመጡ እያንዳንዱን ትራክተር በሦስት ሺህ ብር ከሩማንያ ገዛን በማለት ነበር። በዚህም ምክንያት በአክሲዮኑ ውስጥ ያላቸው ድርሻ በአንዴ ወደ ላይ ተመነጠቀ።

ኢንጂነር ይሄንን አሠራር ይጠራጠሩና የግዢውን ሁኔታ ማጣራቱን ተያያዙት። ሲያጣሩ እያንዳንዱ ትራክተር ከሩማኒያ የተገዛው በአንድ ሺ አምስት መቶ ብር ሆኖ አገኙት። ኢንጂነር "ትራክተሮቹን ያስመጣችሁት በዚህን ያህል ዋጋ ነው። ስለዚህ የእኛ የአክሲዮን ድርሻ እናንተ ቀደም ብላችሁ እንዳስቀመጣችሁት ሳይሆን በዚህን ያህል አድጓል" አሏቸው። ሰዎቹ ምርጫ ስለሌላቸው ኢንጂነር ያሉትን ተቀበሉ። አንድ ጊዜ ደግሞ ጥጥ በብዛት ተመረተ። ሃላፊዎቹ ከጥጥ ፈልቃቂውና ከገዢው ጋር ይሻረኩና "ጥሩ ገንዘብ አግኝተናልና ጥጡን አሁኑኑ እንሽጠው" ብለው ለቦርዱ አቀረቡ።

ኢንጂነሩ ጥጡ በመሸጡ ይስማማሉ። ነገር ግን ዋጋውን ሲያዩት ታች ወርዶ ያገኙታል። ይሄኔ ኢንጂነር ጌታቸው የቦርዱ ስብሰባ

ስለሆኑ ጥጡ በዚህ ዋጋ እንዳይሸጥ ይወስናሉ፡፡ ሰዎቹ የኢንጂነሩን ጥያቄ አስቸጋሪ ለማድረግ "እንግዲያው ጥጡ ሳይሸጥ ቀርቶ ኪሣራ ቢመጣ፣ ለኪሳራው ሃላፊነት ለመውሰድ ብሔራዊ ሃብት ልማት ኮርፖሬሽን ይፈርምልን" አሉ፡፡ ኢንጂነር በራሳቸው በመተማመን ግጥም አድርገው ፈረሙ፡፡

በወራት ውስጥ የጥጡ ዋጋ እላይ ወጣ፡፡ የተገኘውም ትርፍ ከዚህ በፊት ያልታየ አንድ ሚሊዮን ተኩል ትርፍ በመገኘቱ የኩባንያው ካፒታል ወደ ላይ እየተመነደገ ሄደ፡፡

እንግዲህ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ኩባንያው እያደገ ባለበት ሰዓት ነበር የደርግ መንግሥት ብቅ ያለው፡፡





# ምዕራፍ አስር
# ስምንት ዓመት በደርግ እሥር ቤት
# 1966-1975

አብዮቱ እየተቀጣጠለ፣ ወታደራዊው መንግሥትም አምባገነናዊ ሥርዓቱን ለመዘርጋት ሽብ ረብ በሚልበት ሰዓት በየመሥሪያ ቤቱ ባሉ ኃላፊዎች ላይ ወንጀል እየተፈበረከ፣ የነበረም ካለ እየተጋነነ ወሬ በማቀጣጠል ባለሥልጣናት በሙሉ "ይነሱልን፣ ይታሠሩልን፣ ይጠየቁልን" የሚሉ ጩኸቶች በርክተው ነበር፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው የነበራቸውን ንፅህና በመተማመን ጩኸቱን ከቁም ነገር አላገቡትም፡፡ ይሁንና አንድ ጊዜ ግን የአምቦ ውሃ ጥቁር ጠርሙስን በነጭ ለመለወጥ ታስቦ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበር፡፡ የበፊቱ የአምቦ ውሃ ባዶ ጠርሙስ ይመጣ የነበረው ከኤርትራ ነበር፡፡ ከኤርትራ ይመጣ የነበረው ጠርሙስ ብዙ ችግሮች ነበሩበት፡፡ ወደ መሀል ሃገር ሲመጣ መንገድ ላይ ይሠበራል፣ ጠርሙሱ ጥቁር በመሆኑ ለንጹህ ውሃ መገልገያነት አይመችም፣ አቅሙም ደካማ ስለነበር በብዛት ይሰበራል፡፡ እነዚህ ችግሮች ደግሞ ኪሣራን ያስከትላሉ፡፡ ስለዚህ ከዚሁ ከጉለሌ ብርጭቆና ጠርሙስ ፋብሪካ የሚመረተውን ጠርሙስ ለመጠቀም ተወሰነ፡፡ የኤርትራውን ጠርሙስ በጉለሌው ብርጭቆና ጠርሙስ ፋብሪካ ምርቶች ለመለወጥ እንቅስቃሴው ተጀመረ፡፡ በጊዜው የማከፋፈሉ የሥራ ሃላፊ አቶ እንግዳ ጀማነህ የሚባል ሰው ነበር፡፡

በደረሰኝ የተረከባቸውትን ጠርሙስ መልሱና አዲሱን ጠርሙስ

ተረክቡ ተብሎ በሬዲዮ ተነገረ። ሰው የአምቦ ውሃ ጠርሙስ ደረሰኙን አላስቀመጠውም። ጥሎታል። ደረሰኝ ስለሌለው ሕዝቡ ጠርሙስ መለወጥ አልቻለም። አንዳንድ በንግድ ዘርፍ የተሠማሩ ደረሰኝ ያቀረቡ ደረሰኞቻቸውን አቅርበው በማሲያዝ ገንዘባቸውን ተቀብለዋል።

በመካከል የማደያው ክፍል ኃላፊና አንዳንድ ሠራተኞች ጠርሙሱን ከያለበት በአስር ሣንቲም እየሰበሰቡ ከድርጅቱ በማምታታት ወደ ሰባ ሺህ ብር ያህል ለግላቸው ማዋላቸው ተደረሰበት።

በዚህ የማጭበርበር ሂደት ውስጥ የማከፋፈያው ሃላፊ፣ የሂሳብ ሹሙና ሌሎች አከፋፋዮች ገብተውበት ተገኙ። ኢንጂነር ይህንን ሲሰሙ የሹሙን መኪና ነጠቁና ከሥራ አገዱት።

[ጥቁሩን ጠርሙስ ወደ ነጭ የለወጥንበት ብዙ ምክንያቶች ነበሩት ይኸውም፡-

1. የጉለሌው ጠርሙስ ፋብሪካ ውስጥ ከፍተኛው ባለ አክስዮን ስለሆንን ለራሳችን ፋብሪካ ሥራ ለመፍጠር
2. የኛ ጠርሙስ ከአሥመራ ከመጣው ጥንካሬ ያለው ስለሆነ ደጋግመን ልንጠቀምበት ስለምንችል
3. ውሃው ጥራት ያለው ለመሆኑ በግልጽ ስለሚያሳይ ነበር።]

በተባረረው ሰው ምትክ ሌላ ሰው በቦታው እንዲተካ አደረጉ፣ የተባረረው ኃላፊ እድሉን በመጠቀም አከፋፋይ የነበሩትን ሌቦች አስተባብሮ ብዙ የማደያ መኪናዎችን ጭምር አሰልፎ በኢንጂነሩ ላይ ተቃውሞ አስነሳባቸው። ኢንጂነር ምንም ሳይደናገጡ ተሰብ ሳቢው መሀል በመግባት "እናንተ ሌቦች" በማለት ስማቸውን እየጠሩ ሰዎቹን አጋለጧቸው።

እንዲህ እንዲህ ዓይነቱ የሃሰት መነሳሳት እንጂነሩን ከፉኛ





ያበሳጫቸውና ወደ ገንዘብ ሚንስቴር በመሄድ ኃላፊው ዘንድ ቀርበው "ከዛሬ ጀምሮ ሥራውን ለቅቄያለሁ ከሌባ ጋር አል ሰራም። እንዲህ ሲደረግ እያየህ ዝም ብለህ ታያለህ?" ብለው ጠየቁ።

ሃላፊው ለስለስ ብለው "አንተ ዝም ብለህ ፈቃድ ውሰድና ከአከባ ቢው ገለል በል። ነገሩ በዛው ይበርዳል" አሏቸው።

"ይሄ አካሄድ ለተፈጠረው ችግር ትክክለኛው መፍትሄ አይደ ለም። ይልቅ ይሄን ተራ ጨኸትና የሃሰት ክስ አስቁም፤ አለበለዚያ ሥራውን መልቀቄ ነው" በማለት ተናገሩ።

ነገሮች በእንዲህ ሁኔታ እንዳሉ የዕረፍት ፈቃድ ወሰዱ። እናታቸው በዛን ወቅት በጣም ታመው ስለነበረ አባታቸው "እናትህን ለህክምና እንግሊዝ ሃገር ይዘሃት ሂድ" አሏቸው። ኢንጂነር እሺ ይሉና እናታቸውን ይዘው ወደ እንግሊዝ ሃገር ሄዱ።

እንግሊዝ ሃገር ትንሽ እንደቆዩ "The Most Wanted Officials" በጣም የሚፈለጉ ባለሥልጣናት የሚል በጊዜው በደርግ ቁጥጥር ሥር ያልዋሉ ሥም ዝርዝሮች ይመለከታሉ። ዝርዝሩ ውስጥም የእሳቸውን ሥም አገኙት።

"እኔ በፈቃድ ነው የመጣሁት ምን አድርግ ነው የሚሉኝ" ይሉና በግርምታ ለምን ቴሌግራም አልክላቸውም በማለት "እኔ አሁን ያለሁት እንግሊዝ ሃገር ውስጥ ነው። ወደዚህ ስመጣም በፈቃድ ነው። ጉዳዬን ስፈጽም ወደ ሃገሬ እመለሳለሁ" የሚል ይዘት ያለው ቴሌግራም አንዱን በወቅቱ የኢትዮጵያ ጠ/ሚንስትር ለነበሩት ለልጅ እንዳልካቸው መኮንን ፣ ሌላውን ደግሞ ለአራተኛ ክፍለ ጦር ላኩ።

ጠ/ሚንስትር እንዳልካቸው መኮንን ቴሌግራሙ እንደደረሳቸው

“ጉዳይዎትን እንደጨረሱ ሊመለሱ ይችላሉ” የሚል መልዕክት በቴሌግራም ለኢንጂነር ጌታቸው ላኩላቸው።

በጊዜው በእንግሊዝ ሃገር ውስጥ ብዙ ታዋቂ ኢትዮጵያውያኖች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ኢንጂነር ጌታቸው ወደ ሃገር ቤት እንዳይመለሱ መክረዋቸዋል። ያረፉበት ሆቴል ትልቅና ውድም ስለነበረ እነሱ ወዳሉበት ዋጋው ቀለል ወደ አለ ሆቴል እንዲ መጡም ጠይቀዋቸዋል። ሃገር ቤት ያሉ ሰዎችም “አትምጣ” እያሉ ደብዳቤ ጽፈዋል። ኢንጂነር ጌታቸው ግን በስራቸው ንፅህና ስለ ሚተማመኑ ምክሩንም ጥያቄውንም አልተቀበልዋቸውም። ቀደም ብለው ግን እናታቸው እንዳይመለሱ ከልክለዋቸው እዛው ቆይተው ነበር። ይኸውም ኢንጂነሩ አንድ ሕልም አይተው ስለነበር ነው። ያዩትን ህልም ለእናታቸው በነገርዋቸው ጊዜ እናትየው የህልሙን ፍቺ መሰረት አድርገው ኢንጂነሩ በእንግሊዝ ሃገር እንዲቆዩ አጥብቀው ስለመከሯቸው ነው።

ኢንጂነሩ የማንንም ምክርና ማሳሰቢያ ሳይቀበሉ ብድግ ብለው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ከአውሮፕላን እንደወረዱ “የሚፈለጉ ባሥልጣናት” ስም ዝርዝር የያዘ የደህንነት ሠራተኛ ያቆማቸውና “ሥምዎት እዚህ ዝርዝር ውስጥ አለ። አሁን እውጭ ሆነው የሚጠብቅዎት ቤተሰብዎችም እንዳይደናገጡ፣ ከአውሮፕላኑ የወረዱ ሰዎች ከዚህ ወጥተው እስኪ,ቃለል ድረስ እርስዎ እዚች ጥግ ላይ አረፍ ይበሉ” አላቸው። ኢንጂነሩም እንደ ታዘዙት አደረጉ።

እረጋ ያለው የደህንነቱ ሰው የቤተሰባቸውን ሁኔታ የእሳቸውንም ድርጊት ተመልክቶ “አሁን እርስዎን ከዛ ሃገር ድረስ በግድ ያመጣዎት የለም። እራስዎ በፈቃድዎ ነው የመጡት “በማለት





ሃዘን በተጫጫነው ስሜት ጨዋነቱን ከገለጸላቸው በኋላ “የጦር መሣሪያ በተገጠመለት ጂፕ ታጅበው ነበር መወሰድ የነበረብዎት ግን ይህን እኔ አላደርገውም። አንድ የደህንነት ሰው እመድብልዎታለሁ፡ ፡ ከእሱ ጋር እቤትዎ ይሂዱ፣ እቃዎን ያስቀምጡ፣ ከዛ ወደ 4ኛ ክፍለ ጦር ይሄዳሉ” አላቸው። እሳቸውም “መልካም፣ ጥሩ” በማለት ስምምነታቸውን ገለጹ።

ወደ እቤታቸው የወሰዳቸው የደህንነት ሠራተኛ ይበልጥ ጨዋና ሰው አክባሪ ሆኖ አገኙት።

ቀኑ ሥላሴ ስለነበረ፣ እሳቸውም በሥላሴ አጠገብ የቤተ-ክህነት ቤት ተከራይተው የሚኖሩ ስለነበር ሰውዬውን “እባክህን ዛሬ ሥላሴ ነውና ሥላሴን ተሳልመን ወደ ተባለው ቦታ እንሄዳለን” ይሉታል። ሰውዬውም “ግድ የለም እኔ እዚህ እቆይዎታለሁ። ብቻዎን ሄደው ተሳልመው ይመለሱ” አላቸው።

እሳቸውም ወደ ሥላሴ ብቻቸውን ሄደው ፀሎታቸውን አድርሰው ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ማምለጥ ቢፈልጉ ማንም ከልካይ አልነበረባቸውም። ግን አሁንም በራሳቸው ንፅህና በመተማመን አላደረጉትም። እንደተመለሱ የደህንነቱ ሠራተኛ ወደ 4ኛ ክፍለ ጦር ወሰዳቸው።

4ኛ ክፍለ ጦር ግቢ ውስጥ እንደገቡ አንድ ሳሎን የሚመስል ሰፋ ያለ ክፍል ውስጥ አስገቡና አስቀመጧቸው። ትንሽ እንደቆዩ አንድ የጊዜው ባለሥልጣን መጣና ማንነታቸውን አረጋግጦ “ይቆዩ” ብሏቸው ተመልሶ ሄደ።

ወዲያው አንድ ሌላ ባለሥልጣን ወደ እሳቸው መጣ። “ይነሱ” አላቸው። ብድግ አሉ። ለጥያቄ የሚወሰዱ ነበር የመሰ

ላቸው። ሰውዬውን ከተል ብለው ሲወጡ ሁለት ወታደሮች ከፊት፣ ሁለት ወታደሮች ከኋላ ሆነው መሳሪያ ይዘው ያጅቧቸውና ወደ አንድ መኪና አመሩ። መትረየስ የተጠመደባቸው ጂፖች አንድ ከፊት፣ አንድ ከኋላ ሆነው አጀቧቸውና ጉዞ ተጀመረ። ኢንጂነሩ የጂፖቹና የመሣሪያው ጋጋታ አስገርሟቸዋል፣ አስደንቋቸዋል፣ "ክብርም" መሰለኝ ብለዋል።

ታጅበውና በጥብቅ እየተጠበቁ ወደ ፈጥኖ ደራሽ ማሰልጠኛ ተወሰዱ። እዛ እንደደረሱ ክቡር አቶ ይልማ ደሬሳን፣ አባታቸውን ክቡር ብላታ ማህተመሥላሴ ወ/መስቀልንና ወንድማቸውን ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴን አገኙዋቸው። ባለስልጣኖቹ በመስኮት ያመልጡ ይመስል በጥብቅ እየተጠበቁ ነበር።

ሁኔታውን የታዘቡት የቀድሞው የገንዘብ ሚኒስትር አቶ ይልማ የኢንጅነር ጌታቸውን አባት በመገረም "ልጅችዎም ይኸው መጥተዋል፣ ባለቤትዎ እሜቴስ መቼ ነው የሚመጡት?" ብለው በማሳቅ ሁሉንም ዘና አድርገዋቸዋል ይባላል።

ኢንጂነሩ ፈጥኖ ደራሽ ማሰልጠኛ ቢወሰዱም የቀረበላቸው አንድም ጥያቄ አልነበረም። ወደ እዛ በተወሰዱበት መልኩ ከሌሎቹ ባለሥልጣናት ጋር መልሰው ወደ 4ኛ ክፍለ ጦር በበነጋታው እንደወንጀለኛ ወስደዋቸዋል።

ቀጣዩ ተግባር ፀጉር መላጨት ነበርና ሚንስትሮቹን በተራ ቶንዶስ ሙልጭ አድርገው መላጨት እንደጀመሩ ጊዜው ከሰዓት በኋላ ስለነበረ፣ ሦስት ሰዎች ብቻ ላጭተው "በበነገታው ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ" በማለት ፀጉር የሚላጩት ሰዎች ተነስተው ሄዱ።

ልዑል አሥራተ ካሣ በአጋጣሚ አንድ የኤሌክትሪክ መላጫ ቶንዶስ





ይዘው ነበር። ኢንጂነሩ በዚህ የኤሌክትሪክ ምላጭ "ታዲያ እኔ ለምን በደንብ አድርጌ አላጫችሁም" ይሉና ሁሉንም ተራ ሙልጭ ሳላደርግ ቀምቀም አድርጌ ላጭቼ ጨረስኩ።

ፀጉር ቆራጮቹ ጠዋት ፀጉር ሊላጩ ሲመጡ ሁሉም ሰው ተላጭቶ ያገኙዋቸዋል። ተናደዱ። ተበሳጩ። ፀጉር ላጪው ኢንጂነር ጌታቸው በመሆናቸው ትንሽ ፍርሃት ተሰማቸው "ምን አገባህና ነው አንተ ሰዎቹን የምትላጨው?" በሚል ይጣሉኛል በማለት። ግን የእሥረኞቹን ፀጉር በመላጨታቸው ምንም የደረሰባቸው ነገር የለም። እቅዳቸው ባለሥልጣኖቹን እህዝብ ፊት እንደ ወንጀለኛ ፀጉራቸውን በመላጨት ለማዋረድ የነበራቸው እቅድ ሳይሳካላቸው በመቅረቱ የተበሳጩ ይመስል ነበር።

4ኛ ክፍለ ጦር ጥቂት ቀናት እንደቆዩ ምርመራ ተጀመረ። ምርመራው ይህን አጥፍተሃል፣ እንዲህ እንዲህ ዓይነት በደል ፈጽመሃል ወይ ደግሞ ይሄን ያህል የመንግሥት ገንዘብ አጉድለሃል የሚል ዓይነት አልነበረም። ጥያቄው "ምን፣ ምን ሃብት አለህ?" የሚል ነው። "ያቺ ያለችህን ተናግረህ ስታበቃ እንደገና መልሰው "ምን ያደርጋል አሁን ቢደብቁት ነገ እኮ ጉዱ ይወጣል" እያሉ በማስፈራራት ምርመራውን ደጋግመው በተለያዩ መርማሪዎች ይመረምሩ ነበር።

ኢንጂነሩ ሲጠየቁ መስቀል አደባባይ ላይ ከአባታቸው የተሰጣቸውን 1050 ካሬ ሜትር እና ከእናታቸው፣ ቀበና ላይ የደጃች ክፈተው የነበረ፣ ገደላማ የሆነ 1000 ካሬ ሜትር ያገኙ መሆናቸውን አሳወቁ።

ኢንጂነሩ እንደሚሉት ሚንስትሮቹ ሳይቀሩ በባንክ ያላቸው ገንዘብ በግዜው ከአንድ ሺህ ብር እንደማይበልጥ ነው። በእሳቸው በኩል በባንክ ውስጥ ምንም ገንዘብ አልነበራቸውም።

4ኛ ክፍለ ጦር ውስጥ ከታሠሩት እስረኞች መካከል "ከባድ ወንጀለኞች" የሚባሉት እንዲለዩ ተደረገ። ኢንጂነሩ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ሆነው ተመደቡ። እነዚህ "ከባድ ወንጀለኞች" የተባሉት ፍራሻ ቸውን እየተሸከሙ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ተወሰዱ። ሰዎቹ ፍራሻቸውን እየተሸከሙ ከመኪና ላይ ሲያወርዱ፣ መንግሥቱ ኃይለማርያም እራቅ ብለው ተመልክቷቸዋል። ጨለምለም ሲል ነበር የሄዱት። ቤተመንግሥት እንደደረሱም ቁጥር 1 እና 2 ከሚባሉ ክፍል ውስጥ እንዲታጎሩ ተደረገ።

የኢንጂነሩ አባትና ወንድም ከእሳቸው ጋር ቁጥር 2 ውስጥ ገቡ። ቁጥር 1 ውስጥ እነ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሃብተወልድ፣ ፀሃፊ ትዕዛዝ ተፈራ ወርቅ፣ አቶ ማሞ ታደሰ፣ አቶ ከተማ ይፍሩና ሌሎቹም ሚኒስትሮች ታሠሩ።

እሥረኞቹ ምድር ቤት ነበር የታሰሩት፣ ከበላያቸው ደግሞ ደርግ የተለያዩ ስብሰባዎችን ያካሂዳል። ሌላ ጠበቅ ያለ ምርመራ በመርማሪ ኮሚሽንና በተለያዩ የመንግስት አካላት፣ በልዩ ምርመራ ፖሊሶች እሥረኞችን ተራ በተራ በመጥራት ምርመራቸውን አካሄዱ። ውጤት አላገኙበትም። እሥረኞቹን ለመወንጀል ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ ማቅረብ አልቻሉም። አንድ ጊዜ ብቻ ለይስሙላ ሦስት ሰዎችን ባቋቋሙት ልዩ ፍርድ ቤት አቅርበዋቸዋል። ጀኔራል ቀልቤሳን በአመክሮ ለቀዋል። ነፃ ያሏቸውን ሰዎች ግን በመፍታት ፈንታ መልሰው ያሠሩበትም ጊዜ አለ።

"ነፃ ከሆንን ለምን አንለቀቅም" የሚል ጩኸት ያሰማሉ። ይህን ጩኸት ከሚያስተጋቡት ውስጥ አንድ የፓርላማ አባል ነበር። አብ ዝቶ ጮኸ። ወሰዱና ለብቻው ጨለማ ቤት ውስጥ ከተቱት። ጀኔራል





ታደሰን ብቻ ፍርድ ቤት አቅርበው አስፈርደውባቸዋል።

ነገሮች በእንዲህ ዓይነት ከቀጠሉ በኋላ አንድ ቀን ባልታሰበ ሰዓት የእስ ረኞቹ ሃላፊዎች ኢንጂነሩ ወደ ታሠሩበት 1 ቁጥር ክፍል ይመጣሉ። ሲመጡ ሌሎች ሰዎችን ከወህኒ ቤት ይዘው መጥተዋል።

"እገሌ፣ እገሌ" እያሉ ከቁጥር1፣ እና ከቁጥር 2 ክፍል ጠርተው ወደ ውጭ አወጧቸውና እጅና እጃቸውን አቆራኝተው ወደ 60 የሚሆኑትን እሥረኞች ወስደው ጨረስዋቸው።

ይህ አሰቃቂ ድርጊት ከተፈጸመ ከ5 ዓመት በኋላ እንደገና በድንገት ቀን ላይ መጥተው ከእሥረኞቹ መካከል እንዳለፈው ጊዜ የተወሰኑትን ጠርተው ወስደው እልፀል ራስ አሥራተ ካሳ መኖሪያ ቤት ከነበረው በኋላም የደርግ መዝናኛ ከሆነው ቤት ካስገቧቸው በኋላ እንደተሰማው ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው እየጠሩ በሩ ላይ አንገታቸውን በገመድ እያነቁ ከገደሏቸው በኋላ እግቢው አጥር ሥር ለጥበቃ ከተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ የጣሏቸው ለመሆኑ አጽማቸውን ለማውጣት እንቅስቃሴ ሲደረግ ለማወቅ ተችሏል። የኢንጂነር ጌታቸው ወንድም ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመሥላሴም በዕለቱ ለግድያ ከተወሰዱት ውስጥ አንዱ ነበሩ። እነ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ አቶ አሰፋ ድፋዬና ጸሃፊ ትዕዛዝ ተፈራወርቅ፣ ደጃዝማች ካሳ ወልደማርያም ደጃዝማች ስዩም ሃረጎት አቶ አበበ ከበደ ጄኔራል ሳሙኤል በየነ በጠቅላላው 10 ሰዎች ይሆናሉ። የኢንጂነር ጌታቸው ሃዘን በወንድማቸው መገደል ብቻ አልነበረም። አባታቸው ብላቴን ጌታ ማህተመሥላሴ ይታመማሉ። በሽታው ቀላል ነበር። ህክምና ቢያገኙ መዳን ይችሉ ነበር። ህክምና ተከለከሉ። በመጨረሻ ባለቀ ሰዓት ወደ ክሊኒክ ይዘዋቸው ሲሄዱ መንገድ ላይ ህይወታቸው አለፈ።

በአንድ ወቅት በ1986 ዓ.ም ገደማ በቁጥጥር ሥር የዋሉት የደርግ አባላት "ፍትህ ተጓደለብን፣ እኛ አምባገነኖች አይደለንም" በማለት የተናገሩት ንግግር ኢንጂነር ጌታቸውን በጣም አሳዝኗቸውና አስቆጥቷቸው "ተናገር" በሚባል የግል ጋዜጣ ላይ ሰኔ 15 ቀን 1986 ዓ.ም አንድ ጽሑፍ አቅርበዋል። የጽሑፉ ሃሳብ ባጭሩ የሚከተለውን ይመስላል፡-

"1. አባቴን ክቡር ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀልን ያህል ምሁር፣ ለአገር ያገለገሉ፣ ትውልድም ትምህርት የሚያገኝበትንና ታሪኩን የሚያውቅበትን ከ18 በላይ መጽሐፍቶችን የደረሱ የብዙ ቤተሰቦች አስተዳዳሪ የነበሩትን ንጹህና ጨዋ ኢትዮጵያዊ ሃብታቸውን ለመቀማት ስትሉ አስራችሁ ሕክምና በማሳጣት ተሰቃይተው እንዲሞቱ ማድረጋችሁን አትዘነጉም።

2. ወንድሜን ክቡር አቶ ሰይፉ ማህተመ ሥላሴን የመሰሉ ምሁር ለአገራቸው ያገለገሉ ጠንካራ ሠራተኛ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራት ኃይልን ከኩራዝ ደረጃ አንስቶ አሁን ያለበት ሁኔታ ላይ ያደረሱ፣ በሥራ አመራራቸው ማንም ሰው የሚያደንቃቸውን የወደፊት የአገር ገንቢ መሆን የሚችሉትን ኤሌክትሪካል ኢንጂነር አምስት ዓመት በማሰርና ከዚያም በኋላ በድንገት ጠርታችሁ ያለፍርድ በመግደል ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ እንደ ውሻ እሬሳ በአንድ ግለሰብ አጥር ሥር የጣላችሁትን ትረሱታላችሁ?

3. ወንድሜን ጄኔራል በቀለ ማኅተመሥላሴ ገና ለገና የልዑል ጌታዬ አልጋወራሽ የእልፍኝ አስከልካይ ስለሆኑ ሚስጥር ያውቃሉ በማለት ሚሊቴሪ ፖሊስ ውስጥ አስራችሁ በማሰቃየት አልገደላችሁትም?

4. እኔን ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴን ምንም በማላውቀው ሁኔታ ከ8 ዓመት በላይ አስራችሁ ካቆያችሁኝ በኋላ ለአብዮቱ እንቅፋት





ይሆናሉ ተብለው ስለተጠረጠሩ በእስር ቆይተው በምህረት ተለቀዋል በሚል ስትፈቱኝ በ22 አመት የአገልግሎት ዘመኔ ለፍቼ በድካሜ ያፈራሁትን ንብረቴን በሙሉ ወርሳችሁ ለድህነት፣ ለመከራና ለስቃይ ያበቃችሁኝ አንሶ እራሳችሁ ባወጣችሁት አዋጅ መሠረት አንድ የመኖሪያ ቤት እንኳ ተከልክዬ በኪራይ ውስጥ እንድኖር አላደረጋችሁም?

5. ባለቤቴን ዳኛነት ለምን ጠየቅሽ ብላችሁ ለብዙ ግዜ ከማሰራችሁም በላይ እራሳቸውን ያልቻሉ ሁለት ልጆቼን ከመኖሪያ ቤቱ አስወጥታችሁ ቤቱን ለኢሚግሬሽን ቢሮ ስታደርጉ ምትክ እንዳይሰጠኝ አላደረጋችሁም?

6. እህቴ ወ/ሮ ሐረገወይን ማ/ሥላሴን በመንግስት ሥራ ላይ ጨርሶ ያልተሳተፈች መሆኑ እየታወቀ በግፍ ለበርካታ ዓመታት አስራችሁ ካቆያችኋት በኋላ እንድትፈታ ተነግሯት የተሃድሶ ትምህርት ወስዳ እንደጨረሰች መልሳችሁ አላሰራችኋትም?

7. አቶ ሰለሞን ማህተመ ሥላሴ የሚባለውን ወንድሜን በልጅነት እድሜው ባለው የእርሻ ኤክስፐርትነት በየበርሃው በመንገላታት አርሶና ነግዶ ከብዙ ባለሙያዎች ጋር በመወዳደር ያገኘውን ሃብት አስራችሁ ለመውረስ በማደን ላይ እንዳላችሁ አምልጦ በመሰደዱ ቤትና ንብረቱን በሙሉ ወርሳችሁ የናንተ የባለሥልጣኖች መዝናኛ ቦታ ማድረጋችሁን ትክዳላችሁ?

8. ከአባታችን ከክ/ብላቴን ጌታ ማህተመ ሥላሴ ሕጋዊ በሆነ ኑዛዜ የወረስናቸውን በርካታ ቤቶች በፍርደ ገምድል አዋጃችሁ መሠረት ቀምታችሁ አንድ የመኖሪያ ቤት እንኳ ተከልክለን እስካሁን የገዛ ቤታችንን ተከራይተን እንድንኖር አላደረጋችሁም?

9. ለከፍተኛ ትምህርት ውጭ አገር የወጡት ወንድሞቼ፣ እህቶቼና ልጆቻችን ጭምር በእኛ ላይ የደረሰው ግፍ በእነሱም ላይ

እንዳይደርስ በመፍራት ተሰደው እንዲቀሩ አድርጋችሁ የለምን?"

ዓመት፣ ዓመትን እየወለደ ኢንጂነሩ ከታሰሩ ከሥምንት ዓመት ከሁለት ወር በኋላ ተራ ወታደሮች ወደ እሥረኞች ይመጡና "ሁላችሁም ተለቃችኋል" ይሏቸዋል፡፡

የእሥር መለቀቁ ዜና ሲመጣ ኢንጂነር ጌታቸው ከእነ ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ ጋር ሆነው ሻይ እየጠጡ እየተጨዋወቱ ነበር፡፡ ዜናው ግራ አጋባቸው፡፡ በስንት ታንክ የሚጠበቁ ሰዎች ድንገት "ተለቃችኋል ውጡ" ሲባሉ፣ መፈታት ብቻ ሳይሆን፣ ውጡ ብለው ሊያመልጡ ሲሉ ገደልናቸው ቢሉስ የሚል ጥርጣሬ ውስጥ ገቡ፡፡

እውነት መሆኑን ከእሥረኞች መሃል ተጠሪያቸው ካጣሩ በኋላ ከግቢው ለመውጣት ቻሉ፡፡ በኋላ ግን ይጠብቋቸው የነበሩ ወታደሮች ሳይቀሩ እቃቸውን ተሸከሙላቸው፡፡

በወቅቱ ጃንሜዳ ወስደው ነበር የለቀቋቸው፡፡ ሲለቀቁ ብዙዎቹ በእጃቸው ገንዘብ አልነበራቸውም፡፡ አንዳንዶቹ ቤተሰቦች ስለ እሥረኞቹ መፈታት የሰሙ ስለነበሩ ከቤተሰቦቻቸው መኪና መጥቶላቸው ሄዱ፡፡

ኢንጂነር አንድ የሚያውቁት ጀኔራል ያገኛቸውና "በዚህ ተሳፍረህ ሂድ" ብሎ ገንዘብ ሰጣቸው፡፡ በዛ ተሳፍረው ወደ ባለቤታቸው እናት ቤት ሄዱ፡፡

ሁሉ ነገር ተመሰቃቅሎ ነበር ያገኙት፡፡ ንብረት የለ፣ ቤት የለ፡፡ ባለቤታቸውን ከቤታቸው አስወጥተዋቸዋል፡፡ ለኪራይ እንኳን የሚከፍሉት ገንዘብ አልነበራቸውም፡፡

ከዛም ለጊዜው ገነት ሆቴል አንድ ክፍል ተከራይተው መኖር ጀመሩ - ሥራ እስኪያገኙ ድረስ፡፡





# ምዕራፍ አሥራ አንድ
# በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሥራ ቆይታ

ኢንጂነር ጌታቸው ከእስር ቤት እንደተለቀቁ ሥራ መፈለግ ጀመሩ፡፡ የሥራ መጠየቂያ ማመልከቻቸውን ለሦስት መሥሪያ ቤቶች አቀረቡ፡፡ አንዱ ለUNHCR (ለተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን) ሌላው ለFAO (ለዓለም የምግብ ድርጅት) ሲሆን ሦስተኛው ለናይሮቢ ሃቢታት (Nairobi Habitat) ነበር፡፡

ሥራ ለማግኘት ወርም አልፈጀባቸውም፡፡ መጀመሪያ ጠርቶ ያነጋገራቸው FAO ነበር፡፡ አዲስ አበባ ያለው የFAO ሃላፊ ቢሮው ጠርቶ በሰፊው አነጋገራቸው፡፡ "እንደ እናንተ ያሉ ባለሙያዎችና ሰፊ የስራ ልምድ ያላችሁ እዚህ እያላችሁ፣ ለምንድን ነው ከውጭ ሃገራት ባለሙያ ወደዚህ የሚመጡት?" የሚል አስተያየት ጣል አድርገው ነበር፣ የውጭ ሃገር ተወላጅ የሆኑት የሥራ ኃላፊው፣ በኢንጂነር ጌታቸው ሙያና የስራ ተሞክሮ በመደነቅ፡፡ ይህን ከተናገሩ በኋላ "በእርሶ ደረጃ ያሉ ባለሙያዎችን FAO ሲቀጥር እኛ አይደለንም እዚህ የምንወስነው፡፡ እዛው እሮም ያለው ዋናው መስሪያ ቤት ነው የሚወሰነው" ካሉ በኋላ በሁለተኛው ቀን ኢንጂነሩን ጠርተው ያስገቡትን የስራ መጠየቂያ ማመልከቻና፣ የሥራና የትምህርት ሰነድ ወደ ሮም በመላክ እንድንቀጥርዎ እንዲፈቀድልን ጠይቀናል ሲሉ ገለጹላቸው፡፡